በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

# የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሞዴል መመሪያ

(Capital Goods Finance Service Modality)

ጥር 2006 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ማውጫ


መግቢያ ..... 1

ክፍል አንድ ..... 2

1. ራዕይ ..... 2

2. ተልዕኮ ..... 3

3. ዕሴቶች ..... 3

4. ዓላማ ..... 4

5. ዝርዝር ዓላማ ..... 4

6. ትርጓሜ ..... 4

7. መርሆዎች ..... 7

8. የመመሪያው ወሰን ..... 8

ክፍል ሁለት ..... 8

2. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ..... 8

2.1. የግንዛቤ ፈጠራና የማስተዋወቅ ሥራዎች ..... 8

2.2. የገበያ ጥናት ..... 9
2.3. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚዎች ልየታ እና የፍላጎት ጥናት ..... 10
2.3.1. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚዎች ልየታ ..... 10
2.3.2. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚዎች የፍላጎት ጥናት ..... 11
2.4. የማምረቻና መሸጫ ቦታ ዝግጅት ..... 11
2.5. የማምረቻና መሸጫ ማዕከላትን ስለማስተዳደር ..... 12
2.6. ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ ..... 12
2.7. የምርት ጥራት ደረጃ ማረጋገጥ ..... 12

ክፍል ሦስት ..... 14

3. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አሰራር ሥርዓት ..... 14

3.1.1. በሀንድ የዘርፉ አደረጃጀቶችና አሰራሮች ..... 14
3.2. የካፒታል ዕቃ ኪራይ /CAPITAL GOODS FINANCE/ ጠቀሜታ ..... 19
3.3. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶች ..... 19
3.3.1. የዱቤ ግዢ / Hire Purchase/ ..... 20
3.3.2. የፋይናንሺያል ኪራይ /Financial Lease/ ..... 20
3.4. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታዎች ..... 21
3.4.1. ስለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አጠቃላይ ግንዛቤ ማስጨበጥ ..... 21
3.4.2. የንግድ ሥራ ዕቅድ ማቅረብ ..... 22

3.4.3. ስለ ቅድመ ክፍያ ...22
3.4.4. ሕጋዊ ምዝገባ /ንግድ ፈቃድ/ ...23
3.4.5. የሶስተኛ ወገን ውል ስምምነት ...23
3.4.6. የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ...23
3.5. የተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች መስፈርት ...24
3.6. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ስልጠና ...26
3.7. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ...26
3.7.1. የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ማመልከቻ ስለ ማቅረብ ...26
3.7.2. የአዋጭነት ግምገማ ስለ ማካሄድ ...27
3.7.3. የካፒታል ዕቃ ግዢ ቅድመ ሁኔታዎች ...28
3.7.4. የካፒታል ዕቃ ዓይነት እና አቅራቢ ድርጅት ስለ መለየት ...29
3.7.5. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ የብድር ዋስትና ፈንድ በተመለከተ ...30
3.7.6. የመሳሪያ ኪራይ ውል ስምምነት ስለ ማድረግ ...30
3.7.7. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኪራይ አወሳሰን ሥርዓት ...31
3.7.8. የካፒታል ዕቃ ግዢ ስለ ማከናወን ...32
3.7.9. መሳሪያ ማጓጓዝና ምዝገባ ስለ ማከናወን ...33
3.7.10. ኢንሹራንስ መግባት፣ የውል ምዝገባ ስለ ማከናወን እና ስለ ማስተላለፍ ...34
3.7.11. የካፒታል ዕቃ ተከላና ሙከራ ስለ ማከናወን ...35
3.7.12. የካፒታል ዕቃ አጠቃቀም ሥልጠና መስጠት፣ ጥገናና ዕድሳት ስለ ማድረግ 35
3.7.13. ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ስለ ማከናወን ...36
3.7.14. የካፒታል ዕቃ ባለቤትነትን ስለ ማስተላለፍ ...37
3.7.15. ውል የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎችና ቀጣይ የሚወሰዱ እርምጃዎች ...37
3.7.16. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኪራይ አመላለስ ምጣኔ እና የተቋማቱ ቀጣይነት / Repayment rate & Sustainablity/ ...38
3.7.17. የመጋዘን አስተዳደር ሥርዓት / Store Management/ ...39
**ክፍል አራት** ...40
**4. ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎች** ...40
4.1. ለኢንተርፕራይዞች የሚደረጉ ድጋፎች ...40
4.1.1. የሥራ ማስኬጃ ብድር ...40
4.1.2. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ...41
4.1.3. የገበያ ትስስር ...41
4.2. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ የሚደረጉ ድጋፎች ...42
4.2.1. የሎጂስቲክ፣ ትራንዚት እና ከቀረጥ ነጻ የካፒታል ዕቃ የማስገባት አገልግሎት ...42
4.2.2. የማማከር አገልግሎት ...43
4.2.3. የካፒታል ዕቃ እና የግብዓት የብዛት ግዢ አገልግሎት ...44

*4.2.4. የፋይናንስ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ......44*

**ክፍል አምስት ......45**

**5. የፈጻሚና የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ......45**

5.1. ፈጻሚ አካላት ......45
5.2. አስፈጻሚ አካላት ......53
5.3. ባለድርሻ አካላት ......56

**6. የድጋፍና ክትትል ሥራዎች......59**

**7. የመረጃ አያያዝና ሪፖርት ሥርዓት ......61**

**8. ማጠቃለያ ......62**

**9. አባሪዎች......64**

## መግቢያ

ሀገራችን በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ ወሳኝ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ደረጃ በደረጃ በኢንዱስትሪው ለመተካት የሚያስችል መዋቅራዊ ሽግግር ማምጣት ነው፡፡

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት የተለያዩ የካፒታል ዕቃዎችን በፋይናንስ ኪራይ ወይም በዱቤ ግዢ አዲስ ወደ ሥራ ለሚገቡ እና ነባር ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ወስደው የምርት ጥራትና ምርታማነታቸውን በማሳደግ ውጤታማ እንዲሆኑ እና ኢንተርፕራይዞችን የካፒታል ዕቃ ባለቤት ለማድረግ የተዘጋጀ የፋይናንስ ሥርዓት ነው፡፡ የተለያዩ ያደጉ ሀገራት (የዓለም የኢኮኖሚ ልማት ትብብር ድርጅት(OECD) አባል ሀገራት) ይህን የፋይናንስ ሥርዓት እየተጠቀሙበት ሲሆን በእነዚህ ሀገራት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ የግል ኢንቨስትመንቱን አንድ ሦስተኛ ይሸፍናል፡፡ ይህ አሰራር ለተጠቃሚዎች የጎላ ፋይዳ እንዳለው የሀገራቱ ልምድ ያሳያል፡፡ ከእነዚህም መካከል ተጠቃሚው ለማምረቻ መሳሪያ ግዢ ከፍተኛ ገንዘብ ሳያወጣ መሳሪያውን የሚያገኝበት፣ ለሚሰጠው የካፒታል ዕቃ ኪራይ ዕቃውን ያለ ተጨማሪ ዋስትና መጠቀም መቻሉ፣ የቀረጥ ማበረታቻ ማግኘቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰማሩ የጥቃቅን፣ አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና ምርታማነታቸውን በማሳደግ ተወዳዳሪ ለመሆን የመካከለኛ ጊዜ ኢንቨስትመንት የፋይናንስ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ለዚህ ደግሞ ቀዳሚ አማራጭ ሊሆን የሚችለው የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ነው፡፡

ለዚህ ሽግግር መሰረት የሆነውን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በማንፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ትኩረት በመስጠት በዘርፉ የሚታዩትን ማነቆዎች በመፍታት በፍጥነት ወደ ትግበራው በመግባት ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ወሳኝ መሆኑን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂያችን ያመለክታል፡፡

የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ኢንዱስትሪው ዕድገት መሰረት በመሆኑ በዘርፉ የተሰማሩ ጥቃቅን፣ አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንዳያድጉ በተለይም በምርት ጥራት እና ምርታማነትን በማሻሻል ዙሪያ ቁልፍ ማነቆዎችን በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ የተለዩት ዋና ዋና ማነቆዎች

የአመለካከት፣ የማምረቻ መሳሪያዎች፣ የፋይናንስ፣ የማምረቻና መሸጫ ቦታ፣ የቴክኖሎጂና የክህሎት ናቸው፡፡ እነዚህን ማነቆዎች ከመፍታት አንጻር መንግስት በርካታ የማምረቻ ማዕከላት ግንባታ፣ የፋይናንስ ተቋማትን የማጠናከር፣ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ልየታ፣ የክህሎት ስልጠና የማስፋፋት ሥራ ሲሰራ መቆየቱ ይታወሳል፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረቶች እየተደረጉ ሲሆን በዚህም የካፒታል ዕቃዎችን ፋይናንስ አዋጅ እንዲጸድቅ ማድረግ፣ የካፒታል ዕቃዎችን ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ማደራጀት፣ የቴክኖሎጂ ልየታ፣ የማምረቻ ክላስተር ዝግጅትና የኢንተርፕራይዞችን የመምረጥ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በጥቃቅን፣አነስተኛና ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ አቅጣጫ መሠረት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በኢኮኖሚው የሚኖረውን ድርሻ በማሳደግ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስና አቅርቦት አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት ይህን የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የካፒታል ዕቃ አሰራር መመሪያ በአምስት ክፍሎች ተከፍሎ የተዘጋጀ ሲሆን መግቢያ፣ በክፍል አንድ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴት፣ ዓላማ፣ ወሰን፣ትርጉምና የኩባንያው ዝርዝር ዓላማ፣ በክፍል ሁለት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች፣ በክፍል ሦስት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ሥርዓት፣ በክፍል አራት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ሚያስፈልጉ ድጋፎች፣ በክፍል አምስት የፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት፣ የድጋፍና ክትትል ሥራዎች፣ የመረጃ አያያዝና ሪፖርት ሥርዓት እና ማጠቃለያ አካቶ ይዟል፡፡

## ክፍል አንድ

### 1. ራዕይ

በ2025 አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ሥርዓት በመዘርጋት ለኢኮኖሚው ዕድገት ከፍተኛውን ድርሻ የሚያበረክት እና ሰፊ መሠረት ያለው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተፈጥሮ ማየት፡፡

## 2. ተልዕኮ

የምርት ጥራትንና ምርታማነትን የሚያሳድጉ የካፒታል ዕቃዎችን ለጥቃቅን፣ አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ሥርዓት በማቅረብ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ልማት ቀጣይነት ባለው መልኩ በማስፋፋት መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግር ማምጣት ነው፡፡

## 3. ዕሴቶች

**ሐቀኝነት፡-** አክስዮን ማህበሩ የሚሰራውን ስራ ሥነምግባር በተሞላበት፣ በሥርዓት፣ በጥንቃቄ፣ በትጋት፣ በሙሉ ፈቃደኝነት፣ በብቃትና በውጤታማነት ማከናወን፤ እንዲሁም ተቋሙ ለደንበኞች የገባውን ቃል የማክበር፣ ከማታለል ወይም በሙስና ከተዘፈቀ አሰራር ነፃ ሆኖ ማገልገል፤ በተጨማሪም ለሥራ የተመደበውን ሃብትና የስራ ጊዜ ለግል ጥቅምም ሆነ ለሌላ ሰው ጥቅም አለማዋል።

**ታማኝነት፡-** አክስዮን ማህበሩ ለአወጣቸው ህጎች እና ለደንበኞቹ ታማኝ መሆንና ደንበኞችን ሊጎዱ የሚችሉ ማንኛውንም ተግባራት አለመፈጸም፡፡ በህግ ወይም በደንብ ከተቀመጠ የአገልግሎት ክፍያ ውጭ ማንኛውንም ስጦታ ወይም መስተንግዶ አለመቀበል፣

**ግልጸኝነት፡-** አክስዮን ማህበሩ ለደንበኞቹ የሚሰጠውን አገልግሎትና የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በግልጽ የማሳወቅ፣ በሚስጥር መጠበቅ ያለበት ካልሆነ በስተቀር ደንበኞች የሚፈልጉትን መረጃ ከማብራሪያ ጋር መስጠት፡፡

**ቅንነት፡-** ደንበኞችን በመልካም ስነ ምግባርና በቅንነት የማገልገል፡፡

**ተጠያቂነት፡-**አክስዮን ማህበሩ ለሚያከናውናቸው ተግባራትና ለሚሰጣቸው ውሳኔዎች ተጠያቂነትና ኃላፊነት አለበት።

**አድልዎ አለመፈጸም ፡-** አክስዮን ማህበሩ ስራውን ሲያከናውንና አስተያየትም ሆነ ውሳኔ ሲሰጥ አድልዎ መፈጸምና ፍትህን አለማጓደል/። በቀለም፣ በዘር፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በብሄር/ብሄረሰብና በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ ምክንያት ለማንኛውም ደንበኛ የተለየ እንክብካቤ ወይም ልዩነት አለማድረግ። ደንበኛው በሚፈልገው ነገር ላይ ብቻ ተመስርቶ አግባብነት

ያላቸውን ህጎች፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በመከተል ፍትሃዊና ሚዛናዊ የሆነ ውሳኔ ወይም አስተያየት መስጠት።

## 4. ዓላማ

ለኢንዱስትሪው ሰፊ መሠረት የሚጥሉ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ የጥቃቅን፣አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡

## 5. ዝርዝር ዓላማ

- ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት የሚውል የሀብት /resource/ ማፈላለግ እና የፋይናንስ ምንጮችን የመለየት እና ቁጠባ ባህል የሚያሳድግ ሥራዎችን በማከናወን የተቋሙን የፋይናንስ አቅም ማሳደግ፡፡
- የኢንተርፕራይዞችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የካፒታል ዕቃ ግዢ ማከናወን፡፡
- ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት አሰራር የሚያገለግሉ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎችና ማኑዋሎችን በማዘጋጀት የካፒታል ዕቃን ለኢንተርፕራይዞች በውል ማስተላለፍ፡፡
- የካፒታል ዕቃዎች ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞችን አቅም በመገንባት ውጤታማ ማድረግ፣ የካፒታል ዕቃዎችን ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ፤

## 6. ትርጓሜ

**“ማከራየት”** ማለት አከራይ አንድን የካፒታል ዕቃ በፋይናንስ ኪራይ ወይም ወይም በዱቤ ግዥ ስምምነት መሰረት ያለምንም መያዣ በተወሰነ ክፍለ-ጊዜ የሚፈጸም ክፍያ እየተቀበለ ተከራዩ ለተወሰነ ጊዜ ለምርትና አገልግሎት መስጠት ዓላማ እንዲጠቀምበት የሚፈቀድበት በዓይነት የሚደረግ የፋይናንስ አቅርቦት ነው፡፡

**“የፋይናንስ ኪራይ”** /Financial lease/ ማለት አከራዩ

ሀ. ቀደም ሲል ይዞት የሚገኘውን የካፒታል ዕቃ፤ ወይም

ለ. በተከራዩ መራጭነት አቅራቢ ተብሎ ከሚጠራው ሦስተኛ ወገን የሚገዛውን የካፒታል ዕቃ፤ተከራዩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ በሁለት

ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ክፍያ በተወሰነ ጊዜ በመፈጸም እንዲጠቀምበት የሚያከራይበት፣የኪራይ ስምምነት ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ አከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ይዞ የሚቆይበትና የኪራይ ዘመኑ ሲያበቃ ሁለቱም ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ሊገዛ የሚችልበት የኪራይ ዓይነት ነው፡፡

**"የካፒታል ዕቃ"** ማለት ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ማንኛውም መሳሪያ ወይም ማሽን ሲሆን አክሰሰሪዎችን ይጨምራል፣

**"የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ"** ማለት የፋይናንስ ኪራይና የዱቤ ግዥን ማለት ነው፡፡

**"የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበር"** ማለት፡- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስን በኪራይ ሥምምነት መሰረት አንድን የካፒታል ዕቃ ኪራይ እየተከፈለው አንድ ተከራይ እንዲገለገልበት የሚያከራይ የፋይናንስ ተቋም ነው፣

**አቅራቢ፡-** ማለት ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎችን በሀገር ውስጥ አምርተው ወይም ከውጭ ሀገር አስገብተው የሚሸጡ ተቋማት ናቸው፡፡

**መልሶ መውሰድ ማለት፡-** የካፒታል ዕቃ ተከራዩ ግዴታውን በአግባቡ ሳይወጣ ሲቀር አከራዩ የካፒታል ዕቃውን መልሶ መረከብ ማለት ነው፡፡

**መልሶ መረከብ፡-** በፋይናንሺያል ኪራይ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን በመከራየት ክፍያውን ካጠናቀቀ በኋላ የካፒታል ዕቃውን ለመውሰድ ካልተስማማ አከራዩ ዕቃውን መልሶ መውሰድ ማለት ነው፡፡

**ሊሰረዝ የማይችል ሰምምነት፡-** ማለት በህግ አፈጻጸም ወይም በስምምነት ብቻ ካለሆነ በስተቀር ሊሰረዝ የማይችል የኪራይ ስምምነት ማለት ነው፡፡

**ዋስትና፡-** ማለት የካፒታል ዕቃ ኪራይ ክፍያ ባይከፈል በክፍያው ምትክ ሆኖ የሚከፍል ማለት ነው፡፡

**ኢንሹራንስ፡-** ማለት አንድ የካፒታል ዕቃ አደጋ ቢደርስበት ወይም አደጋ ሲያደርስና ጉዳት ሲከሰት ጉዳቱን ካሳ የሚከፍል የመድን ሥርዓት ነው፡፡

**"መዝጋቢ አካል"** ማለት እንደ አግባቡ ንግድ ሚኒስቴር ወይም የካፒታል ዕቃዎችን እና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶችን የመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፤

**“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47/1/ የተመለከቱትን ክልሎች ማለት ሲሆን ለዚህ ማኑዋል አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል፡፡

**“ከተማ”** ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም 2 ሺህ ወይም ከዚህ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡

**“የከተማ አስተዳደር”** ማለት ቻርተር ያላቸውን ከተሞች ሳይጨምር በሌሎች ከተሞች ውስጥ እንደ ማዘጋጃ ቤት ያለ የከተማ አስተዳደርና አገልግሎት እንዲሰጥ የተቋቋመና ራሱን የቻለ አስተዳደራዊ አካል ነው፡፡

**”የክልል ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች”** ማለት በየክልሉ የተዋቀሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ልማት የሚደግፉና የሚያስተባብሩ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች ማለት ነው::

**የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት** ማለት በየከተማው በምርትና አገልግሎት ስራዎች ላይ ለተሰማሩና በተወሰነ አካባቢ ተሰባስበው አንድ ዓይነት ወይም ተመጋጋቢ ምርቶችን በማምረት በጋራ ተጠቃሚ ለመሆን የሚሹ ኢንተርፕራይዞችን ለማስተሳሰርና ለመደገፍ የተደራጁ ናቸው፡፡

**“ክላስተር”** ማለት በአንድ አካባቢ የተሰባሰቡና ቁጥራቸው ከ30 በላይ ሆኖ በ40ኪ/ሜትር ወይም በ1 ሰዓት የመኪና ጉዞ ርቀት ላይ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ሆነው ተመጋጋቢ የምርት፣ የአገልግሎትና የግብዓት አቅርቦት ትስስር ያላቸውና ተመሳሳይ ስጋትና መልካም አጋጣሚውንም የሚጋሩ ተቋማት ስብስብ ነው::

**ጥቃቅን** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤትና የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ እስከ 5 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራ እና ጠቅላላ ንብረታቸው / Total Asset /መጠን በዋጋ መሬትና ህንጻን ሳይጨምር፡-

**በአገልግሎት ዘርፍ** እስከ ብር 50,000 ሃምሳ ሺህ)

**በኢንዱስትሪ ዘርፍ** እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ያለው ኢንተርፕራይዝ ማለት ነው፡፡

**"አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤትና የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራ እና ጠቅላላ ንብረታቸው / Total Asset /መጠን በዋጋ መሬትና ህንጻን ሳይጨምር፡-

**በአገልግሎት ዘርፍ** ከብር 50,001(አምሳ ሽህ አንድ) እስከ 500,000 (አምስት መቶ ሽህ) ያልበለጠ፤

**በኢንዱስትሪ ዘርፍ** ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሽህ አንድ) እስከ 1,500,000(አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ.ህ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

**ታዳጊ ታዳጊ መካከለኛ፡-** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤትና የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ ከ31 በላይሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራ እና ጠቅላላ ንብረታቸው / Total Asset /መጠን በዋጋ መሬትና ህንጻን ሳይጨምር፡-

**በአገልግሎት ዘርፍ** ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሽህ) በላይ፤

**በኢንዱስትሪ ዘርፍ** ከብር 1,500,000(አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ.ህ) በላይ ያለ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

7. **መርሆዎች**

- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ለተመረጡ የስራ ዘርፎች በተለይም ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ለማኑፋክቸሪንግና ኮንስትራክሽን ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ለሌሎች ዘርፎች ሊሰጥ ይችላል፡፡
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስን አሠራር ኢንተርፕራይዞች ያላባቸውን የፋይናንስ ጫና በሚቀንስ መልኩ ይተገበራል፡፡
- የካፒታል ዕቃ ግዥ ሥርዓቱ የጥቃቅን፣ አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ተሳትፎ ያረጋገጠ ይሆናል፡፡
- በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ኢንተርፕራይዙ ተገቢውን ግዴታ ከተወጣ በኋላ ሙሉ በሙሉ የመሳሪያው ባለቤት የሚሆንበት አሰራርን የሚከተል ይሆናል፡፡
- የካፒታል ዕቃ አቅራቢ ተቋሙ በሶስትዮሽ ውል የገበያ ትስስር መሠረት የካፒታል ዕቃ የሚያቀርብበት አሰራር ይፈጠራል፡፡

- በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ መሰማራት ለሚፈልጉ ሴቶች፣ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃንና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡
- በሀገሪቱ የተቀረጹፖሊሲዎችን፣ስትራቴጂዎችን፣መመሪያዎችንና ህጎችን በማክበር ይሰራል፡፡

8. **የመመሪያው ወሰን**

ይህ መመሪያ ተፈጻሚነት የሚኖረው በማኑፋክቸሪንግ እና በኮንስትራክሽን የሥራ ዘርፎች ላይ ለተሰማሩና ለሚሰማሩ የጥቃቅን፣ አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጥ የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የሥራ ዘርፎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች

### 2.1. የግንዛቤ ፈጠራና የማስተዋወቅ ሥራዎች

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ለሀገራችን አዲስ እንደመሆኑ ዓለም አቀፍ ተሞክሮን መሰረት በማድረግ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ህብረተሰቡ እና ተጠቃሚው በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ፣ የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ለሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያለውን አስተዋጽኦ ለማስገንዘብና ኢንተርፕራይዞች ከዚህ አግልግሎት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መስጠት ይገባል፡፡
በዚህም መሰረት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ በየደረጃው ለሚገኙ የዘርፉ ልማት አስፈጻሚ አካላት በጽንሰ-ሃሳቡና በአሰራር ማኑዋል ላይ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን በማመቻቸትና በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ በማድረግ ለኢንዱስትሪው ሰፊ መሰረት ለሚሆነው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ትኩረት ሰጥተው የተቀናጀና ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በማቅረብ ስኬታማ ኢንተርፕራይዞች እንዲፈጠሩ ማድረግ የሚጠበቅባቸው መሆኑን አውቀው እንዲሰሩ መደረግ አለበት፡፡

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦቱን ተግባራዊ ለማድረግ በ4 ክልሎችና በአዲስ አበባ ይህን አገልግሎት የሚሰጡ አክስዮን ማህበራት የተቋቋሙ ሲሆን ማህበራቱ ለተጠቃሚዎች የተቋቋሙበትን ዓላማ እና የሚሰጡትን አገልግሎቶች አስመልክቶ የተለያዩ መድረኮችን፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የህትመት ሚዲያዎችን በመጠቀም ሰፊ የማስተዋወቅ ሥራ በየደረጃው ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ሀገራዊ ፋይዳውን በመረዳት በሚፈጠሩ የተለያዩ የህዝብ ንቅናቄ መድረኮች የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አክሲዮን ማህበሩን የማስተዋወቅ ተግባር ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 2.2. የገበያ ጥናት

ሀገራችን የምትከተለውን የገበያ መር ፖሊሲ መሠረት በማድረግ ማንኛውም ምርት ሲመረት ወይም አገልግሎት ሲሰጥ ከገበያ ጥናት መነሳቱ ሥራው የሚከናወንበትን አከባቢ ንጽጽራዊና አንጻራዊ ጠቀሜታ /competitive and comparative advantage/ ከግምት ውስጥ ያስገባ የገበያ ጥናት በማድረግ የገበያውን ጉድለት ለመሙላት የሚያስችል ስልት በመቀየስ ወደ ትግበራ መገባት እንዳለበት ይታወቃል፡፡

የካፒታል ዕቃዎች አቅርቦት ሥርዓት ሲዘረጋ በቅድሚያ መዳሰስ ካለባቸው ጉዳዮች አንዱ ሥርዓቱ በሚዘረጋበት አከባቢ ገበያው ምን ይፈልጋል የሚለው ጥናት ዋናው ነው፡፡ ምክንያቱም የሚቀርበው የካፒታል ዕቃ የገበያውን ፍላጎት መሠረት እና በአከባቢው የሚገኘውን ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብት ለሥራ ዕድል ፈጠራና ለካፒታል ማከማቻ በማዋል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ስለሚያስፋፋ፣ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች አስተማማኝ ገበያ ካገኙ በኪራይ የወሰዱትን የመሳሪያ ዋጋ በአጭር ጊዜ ውስጥ መክፈል ስለሚያስችላቸው፣ የአከራይ አክሲዮን ማህበሩ ቀጣይነት የሚረጋገጥ መሆኑ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር መቻሉ፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች በስፋት የሚመረቱበት ዕድል መኖሩ እና በሂደትም የቴክኖሎጂ አቅም ክምችት መፈጠር መቻሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት የገበያ ጥናቱ የአካባቢን ዕምቅ ሀብት፣ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትን ተኪ እና ለኤክስፖርት የሚሆኑ የምርት ዓይነቶችን፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥበት አካባቢ ለሚመረቱ ምርቶች የአዋጭነት ጥናት እና ውጤትን

መሠረት በማድረግ በየሥራ ዘርፉ የእሴት ሰንሰለትን ተከትሎ የሚኖረውን የቴክኖሎጂ ክፍተትን አካቶ በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ ፣በቴክኒክና ሙያ ተቋም እና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የሚከናወን ነው፡፡

## 2.3. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚዎች ልየታ እና የፍላጎት ጥናት

### 2.3.1. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚዎች ልየታ

ለማኑፋክቸሪንግ እና ኮንስትራክሽን ልማት ከሚቀርቡ ድጋፎች አንዱ የቴክኖሎጂ (የካፒታል ዕቃ አቅርቦት) ድጋፍ ሲሆን እስካሁን በነበረው ሂደት በዘርፉ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የቴክኖሎጂ አቅርቦት በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ ለመሆን ዋነኛው ግብዓት ቢሆንም ከአቅርቦቱ ውስንነት ጋር ተያይዞ የኢንተርፕራይዞችን ዕድገት በሚፈለገው ደረጃ ሊሆን አልቻለም፡፡ ስለሆነም በቀጣይ ዘርፉ የግብርናውን ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር ዓይነተኛ ሚና ስለሚጫወት ለቴክኖሎጂ አቅርቦት ትኩረት ሰጥቶ መስራት የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለዚህም ዘርፉን ለመደገፍ ካለው ምቹ ሁኔታ እና ቁርጠኝነት የተነሳ ለኢንተርፕራይዞቹ በቂ የሆነ የቴክኖሎጂ የክህሎት እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ለማሟላት በየደረጃው ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህንን ተግባር በአንድ ጊዜ/ወቅት/ ለሁሉም ኢንተርፕራይዞች እና ለሁሉም ዘርፍ ማዳረስ ስለማይቻል በማኑፋክቸሪንግ እና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ የሥርዓቱ ተጠቃሚ የሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች በመምረጥ የማዘጋጀት ተግባር መከናወን አለበት፡፡ ይህም ማለት ኢንተርፕራይዞች በዘርፉ የሚሰጣቸውን ድጋፍ በራሳቸው ላብ እና ክህሎት በመጠቀም ለውጥ አመጣለሁ በሚል ቁርጠኛ መንፈስ ወደ ሥራ ገብተው በትክክልም የኢንዱስትሪ መሠረትነታቸውን የሚያስመሰክሩ እና የልማታዊ ባለሀብትነት አመላከከት የያዙ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ነባርም ሆኑ አዲስ ወደ ሥራ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞችን ተከታታይ በሆኑ የአመለካከት የመለወጥ ሥራ በማከናወን የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ ማምጣታቸውን ማረጋገጥ የፈጻሚ አካላት ድርሻ ነው፡፡

### 2.3.2. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚዎች የፍላጎት ጥናት

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት መሠረት የሚያደርገው የኢንተርፕራይዞችን የካፒታል ዕቃ ፍላጎት በመሆኑ ተጠቃሚ ለሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርበው የካፒታል ዕቃ በሚፈልጉት የሥራ አይነት እና የመሳሪያውን ዝርዝር መግለጫ (Specification) በአካተተ መልኩ በማጥናት አቅርቦቱ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተመረጠው የመሳሪያ አይነት በትክክል ለሚፈለገው የምርት ጥራትና ምርታማነት ለማምጣት የሚያስችል ስለመሆኑ በተለያዩ ባለሙያዎችና በዘርፉ አማካሪዎች የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያሉ የዘርፉን የካፒታል ዕቃ አቅራቢዎች ቀደም ሲል ያሉ ልምዶችን መሠረት በማድረግ የመምረጫ መመዘኛ በማዘጋጀት እና ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር/ቢሮ ካዘጋጀው አጭር ዝርዝር /Short List/ በመነሳት የአቅራቢ ድርጅቶችንም ዝርዝር መረጃ በማሰባሰብ መረጃ የማጠናቀር ሥራ ይከናወናል፡፡ በዚህም መሠረት የተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ፍላጎት ልየታ በዋናነት በአክሲዮን ማህበሩና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጄንሲ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት፣ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት እና የሴቶች፣ ወጣቶችና ህጻናት ጽ/ቤት ይሳተፋሉ፡፡

### 2.4. የማምረቻና መሸጫ ቦታ ዝግጅት

የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ሲቀርብላቸው የማምረቻ ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ቦታው መሠረተ ልማት የተሟላለት በከተማ አስተዳደሩ የተገነባ የክላስተር ማዕከል፣ የኢንዱስትሪ መንደር ወይም ኢንተርፕራይዙ በራሱ ያዘጋጀው ምቹ የማምረቻ ቦታ (በመኖሪያ ቤቱ ወይም በኪራይ) ወይም ተንቀሳቅሰው ለሚሰሩ የሥራ ዘርፎች አድራሻ የሚሆን ቢሮ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር በየክልሉ የኢንተርፕራይዞችን የማምረቻና የመሸጫ ቦታ ችግርን ለመቅረፍ የማምረቻና መሸጫ ክላስተር ማዕከላት እና የኢንዱስትሪ መንደሮችን በመገንባት ለተጠቃሚዎች የማመቻቸት ድጋፍ እየተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህም ኢንተርፕራይዞች ያለባቸውን የቦታና የካፒታል እጥረት ከመፍታት አንፃር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኢንተርፕራይዞቹ

በክላስተር እንዲደራጁና  እርስ በርሳቸው የገበያ፣ የቴክኖሎጂ፣ የስልጠና፣ የጥሬ ዕቃና የካፒታል ዕቃዎች በጋራ የመጠቀም ትስስር እንዲያደርጉ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በመሆኑም ኢንተርፕራይዞቹ እርስ በእርሳቸው በግብዓት አቅርቦትና በምርት ትስስር እንዲፈጥሩ ያስችላል፡፡ ስለዚህም ለሚቀርቡ የካፒታል ዕቃዎች ምቹ እና ደረጃውን የጠበቀ የማምረቻ ቦታ መዘጋጀት አለበት፡፡

## 2.5. የማምረቻና መሸጫ ማዕከላትን ስለማስተዳደር

በክልል እና በከተማ አስተዳደሮች የተገነቡ ክላስተር ማዕከላትን በክልል መንግስታት ውሳኔ መሠረት የካፒታል ዕቃ አቅራቢ ተቋሙ ከካፒታል ዕቃው ጋር በማከራየት እንዲያስተዳድር ይደረጋል፡፡

## 2.6. ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ

አንድ ኢንተርፕራይዝ የራሱን ሥራ ፈጥሮ ውጤታማ ለመሆን ሲያስብ በቅድሚያ የኢንተርፕርነርሺፕ ክህሎት በአግባቡ መላበሱን እርግጠኛ መሆን አለበት፡፡ ይህም የሚሆነው ተከታታይነት ያለው ስልጠና ማግኘት ሲችል ነው፡፡ ኢንተርፕራይዞች ስለሚያመርቱት ምርት አመራረት ሂደት፣ ጥራትና ምርታማነት በቂ ዕውቀት ጨብጠው ወደ ሥራ እንዲገቡ  ለማድረግ የቴክኒክ ክህሎት ስልጠና ቁልፍ መሳሪያ ሲሆን የሚጠቀሙበትን ማምረቻ መሳሪያዎች አጠቃቀምና አያያዝ በቂ ዕውቀትና ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ያመረቷቸውን ምርቶች ወደ ገበያ አውጥተው ለመሸጥና አዳዲስ የምርት ዲዛይኖችን እንዲዘጋጁ የሚያስችል የንግድ ሥራ አመራር ስልጠና ውጤታማ ለመሆን መሠረት በመሆኑ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት  በተከታታይ ሊሰጣቸው የሚገባ ድጋፍ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት የሚሰጡ ሆኖ በየከተሞቹ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እያንዳንዱን ምርት ለማምረት የሚያስችል በቂ የክህሎት ሥልጠና መስጠት የሚያስችሉ ተቋማት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

## 2.7. የምርት ጥራት ደረጃ ማረጋገጥ

ኢንተርፕራይዞች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ገበያ ምርትና አገልግሎታቸውን ይዘው ሲቀርቡ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን የሚፈልገው ደምበኛ በሚፈልገው እና

ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሚያስቀምጡት ደረጃ አቅርቦቱ መፈጸም እንዳለበት ይታመናል፡፡ ስለዚህም ኢንተርፕራይዞች ለሚያመርቱት ምርትና ለሚሰጡት አገልግሎት አሰገዳጅ ደረጃ ያላቸው ከሆነ ከንግድ ሚኒስቴር፣ከኢትዮጲያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት እና ከኢትዮጵያ የምግብ ፣ የመድኃኒት አስተዳደር እና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም የአስገዳጅ ደረጃ ያላቸውም ምርቶች የሚመረትባቸው መሳሪያዎች ደረጃ /Grade/ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ አስገዳጅ ያልሆነ ደረጃ የሚወጣለቸው ምርቶች በሂደት በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ደረጃ የሚወጣላቸው ሆኖ በመጣላቸው ደረጃ መሠረት በኢነንተርፕራይዞች የሚመረቱ ምርቶች በተስማሚነት ምዘና ድርጅት ማረጋገጫ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡ የምርት እና የማምረቻ መሳሪያዎች ጥራት ደረጃን በሚመለከት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአስፈጻሚ አካላት እና ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ተከታታይ የሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላሉ ምርቶች የተጠቃሚውን የመግዛት አቅም መሠረት በማድረግ ደረጃ እንዲወጣላቸው ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር በጋራ የሚሰራ ይሆናል፡፡ የምርት ጥራቱ ከሚረጋገጥባቸው ግብዓቶች አንዱ ደረጃውን የጠበቀ የካፒታል ዕቃ መጠቀም መቻል ነው፡፡ በመሆኑም የካፒታል ዕቃ አቅራቢ አክሲዮን ማህበሩ የሚያቀርበው የካፒታል ዕቃ ዘመናዊ እና ደረጃውን የጠበቀ ምርት ማምረት የሚያስችል መሆን ይገባዋል፡፡

## ክፍል ሦስት

### 3. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አሰራር ሥርዓት

በሀገራችን የጥቃቅን፣ አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ያለባቸውን የማምረቻ መሳሪያዎች እጥረት ለመቅረፍ መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ በክልሎችና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማምረቻ መሳሪያ የሚያቀርቡ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አክስዮን ማህበራት እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን ይህንን ሥርዓት በስፋት ተግባራዊ ለማድረግ የውጭ ሀገር ተሞክሮችን ለመውሰድ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት በህንድ፣ ስሪላንካ እና ሞሪሽየስ ሀገራትን ልምድ የተወሰደ ሲሆን በተለይም ከህንድ አገር ተሞክሮ ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ትግበራ ጉልህ ድርሻ ያላቸውን ጉዳዮች ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

### 3.1. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት የህንድ አገር ተሞክሮ

#### 3.1.1. በህንድ የዘርፉ አደረጃጀቶችና አሰራሮች

በህንድ ለዘርፉ ድጋፍ እንዲያደርግ የተቋቋመው የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ አንተርፕራይዞች ሚኒስቴር ሲሆን በስሩ ለኢንተርፕራይዞቹ በቀጥታ ድጋፍ የሚያደርጉ በርካታ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል

- Development commissioner MSME,
- National Small Industry corporation

- Khadi and Village Industries commission
- Central Coir Research Institute
- National Institute for MSME
- Entrepreneurship and Small Business Development
- India Institute of Entrepreneurship

እነዚህ ተቋማት ኢንተርፕራይዞቹን ለመደገፍና ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ድጋፎች ይሰጣሉ፡፡ ከድጋፎቹም መካከል የገበያ ድጋፍ አገልግሎት /Marketing Support Service/ የብድር ድጋፍ አገልግሎት /Credit support Service/ የቴክኖሎጂ ድጋፍ አገልግሎት /Technology Support Service/ የኢንኩቤሽን ማዕከል አገልግሎት /Incubations Center Service/ የኢንተርፕሩነርሽፕ እና የመሠረተ ልማት አቅርቦት ድጋፎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በሀገሪቷ ከ31 ሚሊዮን በላይ ኢንተርፕራይዞች ሲኖሩ በመቶኛ ድርሻቸው ጥቃቅን 94% አነስተኛ 0.17% መካከለኛው 4.89% ነው፡፡ እነዚህ ኢንተርፕራይዞች ከ600 በላይ የሚሆኑ የምርት አይነቶችን የሚያመርቱ ሲሆን በስራ ዕድል ፈጠራም ከ73 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች በዘርፉ ተሰማርተዋል፡፡ በሀገሪቱ ከግብርና ቀጥሎ በርካታ ሰዎች በዘርፉ የተሰማሩበት ነው፡፡

ኢንተርፕራይዞቹ እ.ኤ.አ በ2007 ዓ.ም 143 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ እ.ኤ.አ በ2011 ዓ.ም 200 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚጠጋ ምርት ያመረቱ ሲሆን በአለም አቀፍ የኢኮኖሚ ቀውስ በተከሰተበት ወቅትም ቢሆን አመታዊ አማካኝ ዕድገቱ 10% ነበር:: በሀገሪቱ ካሉት ኢንተርፕራይዞች 45% በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰማሩ ሲሆን ከሚያመርቱት ምርት 40% ለኤክስፖርት ገበያ ያቀርባሉ፡፡ ይህም ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 8% ድርሻ አለው፡፡

ለኢንተርፕራይዞቹ በርካታ ባንኮችም የብድር እና የተለያዩ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡፡ በተለይም ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ የሚሠጥ ልማት ባንክ /Small Industries Development Bank/ ተቋቁሞ ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መጠነ ሰፊ የፋይናንስ አቅርቦት ድጋፍ፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ለዘርፉ ድጋፍ የሚያደርጉ የፋይናንስ ተቋማትን የማስተባበር ሥራዎች ያከናውናል፡፡ በመንግስት ከተቋቋሙት በተጨማሪ በርካታ የግሉ ዘርፍ ተቋማትም በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ

ሥራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ የሀገሪቱ መንግስት የካፒታል ዕቃ የፋይናንስ አገልግሎቱን ለማሳለጥ የተለያዩ አዋጆችና ህጎች አውጥቷል፡፡ ከነዚህም መካከል

- Reserve Bank of India Act 1943 in case of involvement of NBFCs
- Foreign Exchange Management Act (FEMA Laws)
- Foreign Direct Investment (FDI) Rules in case of companies having FDI
- Sale of Goods Act, 1930
- Indian Contract Act, 1872
- Transfer of Property Act, 1882
- Income Tax Act, 1961
- Limitation Act, 1930
- Indian Stamp Act, 1899
- Arbitration Act, 1940
- VAT Rules
- Hire purchase Act,1972 ናቸው፡፡

የካፒታል ፋይናንስ ተቋማት በዓመት የሚሰጡት የሊዝ አገልግሎት እስከ 3.6 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር የሚደርስ ሲሆን አገልግሎት የሚሰጡበት ዘርፍም በዋናነት

- ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች
- ለመሠረተ ልማት ዘርፍ /ለመንገድ ስራ፣ ኮንስትራክሽን የሚያገለግሉ ትላልቅ ማሽነሪዎች (Earth moving and construction)
- ለነዳጅና ጋዝ እንዲሁም ለማዕድን ቁፋሮ የሚውሉ ማሽነሪዎች
- ለአውሮፕላን ማረፊያዎችና የባቡር መንገዶች ግንባታ የሚውሉ ትላልቅ ማሽነሪዎች
- በቴክኖሎጂና የህክምና ሴክተሮች አገልግሎት ላይ የሚውሉ የስራ ማሽነሪዎች
- ለገጠር መሠረተ ልማት ግንባታ ወዘተ የሚውሉ ማሽነሪዎች ላይ ነው፡፡

### 3.1.2. የካፒታል ፋይናንስ ተቋሞቹ ዋና ዋና የአሰራር ስልቶች

ሀ. የፋይናንስ ተቋሞቹ ለአነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በፋይናንሺያል ሊዝና በዱቤ ግዥ ፋይናንስ ከሚሰጠው የማሽነሪና የካፒታል ዕቃዎች በተጨማሪ በዋነኝነት በመሠረተ ልማት ዘርፍ

ለተሠማሩ ትላልቅ የንግድ ኩባንያዎች ተመሳሳይ አገልግሎት መስጠት፣ እንዲሁም ከመሣሪያ ሊዝና የዱቤ ግዥ አገልግሎት በተጨማሪ በማማከርና በኢንቨስትመንት ስራዎች መሰማራታቸው በዚህም የተቋማቸው የገቢ ምንጭ እንዲሰፋ ማድረጋቸው፣

ለ. ተቋሞቹ በሊዝና በዱቤ ግዥ ፋይናንስ ለሚሠጧቸው የፋይናንስ አገልግሎት በዋነኝነት ለዚሁ አገልግሎት የተገዙትን መሣሪያዎች በዋስትና የሚይዙ ሲሆን እንደ ፋይናንስ ክብደቱ መጠን እየታየ ተጨማሪ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በዋስትና የሚይዙ መሆኑ፣

ሐ. ከመሣሪያ ሊዝና የዱቤ ግዥ ፋይናንስ በተጨማሪ ለስራ ማስኬጃ የሚሆን በተወሰነ ጊዜ ተከፋይ የሚሆን ብድር (Term Loan) የሚሰጡ መሆናቸው፣

መ. የመሣሪያ ሊዝና የዱቤ ግዥ ፋይናንስ እንደመሣሪያው ዓይነት እየታየ ከ3-5 ዓመታት የሚቆይ የሊዝ አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑ፣

ሠ. ለመሣሪያ ግዥ ከሚያስፈልገው ዋጋ ውስጥ ከ75-85% ብቻ ፋይናንስ ማድረግና ልዩነቱ በደምበኛው በሚደረግ የቅድሚያ ክፍያ እንዲሸፈን ማድረጋቸው፣

ረ. የመሣሪያ ሊዝ አገልግሎት ደምበኞች ስለሚወስዱት መሣሪያ አጠቃቀም አያያዝ፣ መለስተኛ ጥገናና የመለዋወጫ ዕቃዎች (Spare Parts) አስመልክቶ አስፈላጊውን የንድፈ ሃሳብ እና የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ የሚያደርጉ መሆናቸው፣

ሰ. የፋይናንስ ተቋማቶቹ ደምበኞች ዘንድ ለመድረስ የሚጠቀሙባቸው ስልቶች ፣

- በማስታወቂያዎች፣ በፎርሞችና በመሳሰሉት ለደምበኞች ስራዎቻቸውን በማስተዋወቅ፤ የካፒታል ዕቃዎች አምራች ድርጅቶች ለሚያመርቱት ዕቃዎች ገዥ በማፈላለግ ለብድር አገልግሎቱ ደምበኞችን ወደ ባንኩ በመላክ፣
- ደምበኞች በቀጥታ ወደ ተቋሞቹ በመምጣት አገልግሎቱን ማግኘትና ወዘተ ናቸው፡፡

ሸ. ተቋማቱ በፋይናንሺያል ሊዝ ለሚሰጧቸው የካፒታል ዕቃዎች የአገልግሎት ቅናሽ (Depreciation) በአከራዩ የሂሳብ መዝገብ እንዲመዘገቡ መደረጉና

እንዲሁም በህንድ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መሠረት ተከራዩ በሂሣብ መዝገቡ ካፒታላይዝ (Capitalize) አድርጎ እንዲመዘገብ በማድረግ ማስተናገዳቸውና የአገልግሎት ቅናሹም (Depeciation) በተከራዩ መዝገብ እንዲመዘገብ መደረጉ ናቸው፡፡

ቀ. የካፒታል ዕቃ የሚያመርቱ/የሚያቀርቡ ተቋማትን በመለየት ተመዝግበው የሚያዙ መሆኑ

በ. የብዛት ግዢ በNSCI በኩል ለ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርብ መሆኑ

ተ. ለኢንተርፕራይዞች የምርት ጥራት ምዘና እና የአፈፃፀም ደረጃ (rating) ማውጣት ዋና ዋና ዎቹ ናቸው፡፡

### 3.1.3. የዕፎይታ ጊዜ የክፍያ ጊዜ እና አከፋፈል ሁኔታ

የዕፎይታ ጊዜ፡ የክፍያ ጊዜና የአከፋፈል ሁኔታ በአዲስ ኢንተርፕራይዝ እና በነባር ኢንተርፕራይዝ እንዲሁም በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፍ የተለየ ነው፡፡

የዕፎይታ ጊዜ፣የክፍያ ጊዜ እና አከፋፈል ሁኔታ ፡-

| | ኢንዱስትሪ | አገልግሎት |
|---|---|---|
| አዲስ ኢንተርፕራይዝ | | |
| የዕፎይታ ጊዜ | ከ6-12 ወር እንደ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት (cash flow) የሚወሰን | 6 ወር |
| የክፍያ ድግግሞሽ ብዛት (የሩብ ዓመቱ) | 20 ጊዜ | 20 ጊዜ |
| የክፍያ ዘመን | 5 ዓመት | 5 ዓመት |
| ነባር ኢንተርፕራይዝ | | |
| የዕፎይታ ጊዜ | 6 ወር | 6 ወር |
| የክፍያ ጊዜ ብዛት ( በየሩብ ዓመቱ) | 20 ጊዜ | 20 ጊዜ |
| የክፍያ ዘመን | 5 ዓመት | 5 ዓመት |

ተቋማቶቹ በወቅቱ ለሚከፍሉ ኢንተርፕራይዞች፣ በቅድመ ክፍያ መጠን ላይ ለሴቶችና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ ማበረታቻዎች አሏቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት የህንድ ተሞክሮን ስንመለከት ሀገራችን አሁን ካለችበት የእድገት ደረጃ አንጻር ብዙ የሚቀር እና የተሻለ ተሞክሮ ካላቸው ሀገራት ልምድን በመቀመር ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም በማድረግ የተለያዩ የአሰራር ሥርዓቶች አና ስልቶችን ነድፎ ወደ ትግበራ መግባት ወሳኝ በመሆኑ የህንድ ሀገር ልምድን ለዚህ ማኑዋል ዝግጅት እንደ ግብዓት መጠቀም ተችሏል፡፡

## 3.2. የካፒታል ዕቃ ኪራይ /capital goods finance/ ጠቀሜታ

- የካፒታል ቁጠባ፡- ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን በኪራይ በማግኘቱ ያለውን ካፒታል ለሌላ የምርት ተግባር የሚያውለው ስለሆነ ለካፒታል ቁጠባ ጠቀሜታ ይኖረዋል፣
- የተከራዮችን ሁኔታና ፍላጎት መሰረት ያደረገ የክፍያ መጠንና የክፍያ ጊዜ ስምምነት ማድረግ የሚቻል መሆኑ፣
- የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ዕቅድ፡- ተከራይ የጥሬ ገንዘብ ፍሰቱን በዕቅድ እንዲመራ ያስችላል፣
- የገንዘብ አቅምን ማሻሻል፡- የተከራይን የሽያጭ ሁኔታ የመክፈያ ጊዜን ዘዴዎችን በመጠቀም የገንዘብ የመኖር አቅምን ያሻሽላል፡፡
- የካፒታል ኢንቨስትመንት እንዲነቃቃ ከማድረጉ ባሻገር በመጠኑ ያገለገሉ የካፒታል ዕቃዎች ገበያ እንዲኖር ምክንያት ይሆናል፡፡

## 3.3. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶች

በአገራችን የካፒታል ዕቃ ፋይናንስን ሥርዓትን እንዲተገብሩ በብሔራዊ ባንክ ፍቃድ የተሰጠው ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አክስዮን ማሕበር ነው፡፡ በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ የተፈቀደው የኪራይ ዓይነቶችም የዱቤ ግዢ / Hire Purchase/ እና የፋይናንስ ኪራይ ናቸው፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የካፒታል ዕቃ ባለቤት ለማድረግ በዋነኝነት በዱቤ ግዢ ሥርዓት የሚተገበር ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ የፋይናንሺያል ኪራይ ተግባረዊ ሊሆን ይችላል፡፡

### 3.3.1. የዱቤ ግዢ / Hire Purchase/

ይህ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ዓይነት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ስራ አዋጅ ቁጥር 103/19190 በተፈቀደው መስረት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ አይነት ሆኖ፡-

- አከራይና ተከራይ ባደረጉት ስምምነት መሰረት አከራይ በተወሰነ ጊዜ የሚደረግ ክፍያ እየተከፈለው አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃ ተከራዩ እንዲጠቀምበት የሚፈቅድበት፣
- እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ በተደረገ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ ለተከራዩ የባለቤትነት መብት የሚተላለፍበትና
- ተከራዩ የመጨረሻውን ክፍያ እንደፈጸመ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ወዲያዉኑ የሚያገኝበት የኪራይ ዓይነት ነው፡፡

የኪራይ ስምምነቱ ባህሪያት በአዋጁ እንደተጠቀሰው የዱቤ ግዢ ኪራይ ስምምነት የሚከተሉት ባህርያት ይኖሩታል፡-

- እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ በተፈጸመ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ የባለቤትነት መብት እንዲሁም የመጨረሻ የኪራይ ክፍያ እንደተፈጸመ ወዲያውኑ የካፒታል ዕቃው ሙሉ በሙሉ የባለቤትነት መብት ለተከራዩ የሚተላለፍለት ይሆናል፡፡ የማስተላለፊያ ሂደቱም በዚህ ማኑዋል መሰረት ይሆናል፡፡
- የመድህን ዋስትና የመግባትና እና በየአመቱ የማደስ የተከራዩ ኃላፊነት ነው፣
- አቅራቢው ከሰጠው የዋስትና ጊዜ በኋላ የጥገና ተግበራት የማከናወን ኃላፊነት የተከራይ ነው፡፡

### 3.3.2. የፋይናንሺያል ኪራይ /Financial Lease/

የኪራይ ስምምነቱ የሚከተሉት ባህርያት ይኖሩታል፡

- ተከራዩ የኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ሁሉ የካፒታል ዕቃውን በአግባቡ እንዲጠቀምበት የውል ስምምነት ይገባል፤
- ተከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ምንም አይነት የባለቤትነት መብት የለውም፤

- ስምምነቱ ውል የተገባለትን ሙሉ ዋጋ በኪራይ ተከፍሎ የሚሸፈንበትና ሊሰረዝ የማይችል ስምምነት ነው፤
- የስምምነቱ ጊዜ ሲያበቃ ሁለቱ ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ በስምምነቱ መሠረት የካፒታል ዕቃውን ይረከባል ካልተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ለአከራዩ ይመልሳል፤
- ተከራዩ ለካፒታል ዕቃው መድህን የመግባትና ተገቢውን ዕድሳት በወቅቱ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤
- የካፒታል ዕቃው በተገቢው መንግስታዊ አካል ይመዘገባል፤
- አቅራቢው ከሰጠው የጥገና ዋስትና/ warranty/ Guaranty/ ጊዜ በኋላ የጥገና ተግባራት የማከናወን ሃላፊነት የተከራይ ነው፡፡

## 3.4. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታዎች

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ለሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡፡

### 3.4.1. ስለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አጠቃላይ ግንዛቤ ማስጨበጥ

- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ/ቢሮ/የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ/ቢሮ / ኮሚሽን/ እና በአንድማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አማካኝነት፡-
    - ስለ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ጠቀሜታ
    - እንዴት አገልግሎቱን ማግኘት እንደሚችሉ፤
    - እንዴት የንግድ ሥራ ዕቅድ ማቅረብ እንዳለባቸው እና
    - የአሰራር ሂደቱን ግንዘቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
- በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አክስዮን ማህበሩ በኩል፣
    - ስለ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ፣
    - ስለ ካፒታል ዕቃ አጠቃቀም፤
    - ስለሚያስፈልገው የቅድመ ክፍያ መጠን፣
    - ስለሚሰጥ የካፒታል ዕቃ የገንዘብ መጠንና የዋስትና አይነት፣
    - ስለሚከፈል የወለድ/ የኪራይ መጠንና አገልግሎት ክፍያ፣

- ስለ መድህን ሽፋንና የመሳሪያ ጥገና፣
- ስለ አከፋፈል ሁኔታ እና አጠቃላይ ስል አክስዮን ማህበሩ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

### 3.4.2. የንግድ ሥራ ዕቅድ ማቅረብ

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ስለሚሰሩት ሥራና የአዋጭነት ሁኔታ የሚገልጽ የንግድ ሥራ ዕቅድ በስታንዳርድ ፎርማት መሠረት በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ኤጀንት ድጋፍ አማካይነት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የንግድ ሥራ ዕቅዱም የሥራ ማስኬጃ፣ የሥራ ቦታንና የካፒታል ዕቃ ፍላጎትን ባካተተ መልኩ ወይም በተናጥል እንደ ተጠቃሚው ፍላጎት መሠረት ሊቀርብ ይችላል፡፡ የንግድ ሥራ ዕቅድ ሊይዝ የሚገባው ዋና ዋና ነጥቦች፡-

- የአግልግሎቱ ተጠቃሚ አጠቃላይ መረጃ/ ፕሮፋይል፤
- ኢንተርፕራይዙ ስላለው ሃብት፤
- በቀጣይ ስለሚኖረው የገቢና የወጪ ሁኔታ መግለጫ፤
- የድርጅቱን የሥራ ሁኔታ ወይም የማምረት ሂደት፤
- ተጠቃሚው ማህበር ከሆነ የማኅበሩ አባላት ብዛትና የማምረቻ መሳሪያ አጠቃቀም ሥርዓት/ የሰራተኞች ብዛት፤
- የካፒታል ዕቃው የሚሰጠው አገልግሎት፣ ያለው የሥራ ቦታ፣ ጥሬ ዕቃ አቅርቦት ሁኔታ፤
- የኪራይ ተጠቃሚው ዋና ዋና ንብረቶች፣በአበዳሪ ተቋማት ያለው የብድር ታሪክ፤
- የሥራ ተሞክሮ እና የቴክኒክ ብቃቱን ወይም ስልጠና የሚያሳይ ማስረጃ፤

### 3.4.3. ስለ ቅድመ ክፍያ

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ መሠረት ተጠቃሚው በንግድ ሥራ ዕቅዱ የተቀመጠውን መነሻ ካፒታል ከ 15 እስከ 20 በመቶ ቁጠባ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚያስቀምጥ ሆኖ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተቋሙ ቅድሚያ ክፍያውን በሚፈልግበት ጊዜ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ በኤክስፖርት እና ተኪ ምርቶችን ለሚያመርቱ ኢንተርፕራይዞች  የካፒታል ዕቃውን ዋጋ 15 በመቶ

በሌሎች የስራ ዘርፍ ለሚሰማሩ 20 በመቶ ተጠቃሚው እንዲያቀርብ በማድረግ ለአቅራቢው እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ከማስፋፋት አንጻር በከፍተኛ ካፒታል ተገንብተው ለተጠቃሚዎች የሚተላለፉ ፋብሪካዎች (Turn key) እና አስተማማኝ ገበያ ያላቸው ምርቶችን ለሚያመርቱ ኢንተርፕራይዞች ያለ ቅድመ ክፍያ ይስተናገዳሉ፡፡፡፡

- የተከራዩ ዕዳ የሚሆነው የከፈለው ቅድመ ክፍያ ተቀንሶ ይሆናል፤
- ተከራዩ መሳሪያው እንዲገዛለት በጠየቀው መሰረት የካፒታል ዕቃው ተገዝቶለት አልወስድም የሚል ከሆነ፣ የአጠቃላይ የካፒታል ዕቃውን ዋጋውን 5 በመቶ ቅጣት እንዲከፍል በማድረግ የከፈለውቀሪ ገንብ ይመለስለታል፡፡

### 3.4.4. ሕጋዊ ምዝገባ /ንግድ ፈቃድ/

በጥቃቅን አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ሥራ ላይ የሚሰማራ ግለሰብ ወይም የንግድ ማህበር የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን በቅድሚያ ወደ ሥራው ሊያሰማራው የሚችል ህጋዊ ምዝገባ ( የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርና የንግድ ፈቃድ/ ሊኖረው ይገባል፡፡

### 3.4.5. የሶስተኛ ወገን ውል ስምምነት

የሦስተኛ ወገን ለተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ሥራ በሚሰጥበት ወቅት የሥራ ውል ሥምምነት መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ያለምንም ቅድመ ክፍያ ለተጠቃሚው እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

### 3.4.6. የመስሪያና የመሸጫ ቦታ

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን በቅድሚያ የመስሪያ እና የመሸጫ ቦታ ስለመኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

### 3.4.7. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት የሚተገበርባቸው የማኑፋክቸሪነግ ዘርፎች

- ጨርቃ ጨርቅና  አልባሳት፣ ሽመናና ስጋጃ ሥራ፣ ልብስ ስፌት
- የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ሥራ
- የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ሥራ

- አግሮ ፕሮሰሲንግ

## 3.5. የተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች መስፈርት

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከዚህ በታች የተቀመጡትን የመመልመያ መስፈርቶች ማሟላት የሚጠበቅባቸው ሲሆን የሚመለምለውና የሚያደራጀው አካል (የአንድ ማዕከል አገልግሎት/ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ/ቢሮ/ መስፈርቶቹ መሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡ እንዲሁም የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መረጃ አስመልክቶ የከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ጽ/ቤት/ተቋማት፣ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት፣ የሴቶችና ወጣቶች ጽ/ቤት እና የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አክሲዮን ማህበሩ በጋራ መለየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች የሚከተሉትን ሁኔታዎችን ሲያሟሉ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

- ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶች በሚተኩና የኤክስፖርት ምርቶችን ለሚያመርቱ፤
- በክላስተር ማዕከላት በመሰባሰብ በተመረጡ የስራ ዘርፍ ላይ ተሰማርተውና በሞዴልነት ተመርጠው ስራቸውን ለሚያከናውኑ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ፈላጊዎች  በተመረጡ የሥራ ዘርፎች ላይ ለሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ግዢ ለማከናወን የሚያቀርቡት የንግድ ሥራ ዕቅድ አዋጭነት  የሚገመገም ሆኖ፡-
    - መሣሪያውን ለመጠቀም በቂ ሥልጠና የወሰዱ፤
    - ለሚያመርቱት ምርት በቂ ገበያ ያላቸው ፤
- ነባር ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስቀድመው ከማንኛውም አበዳሪ ተቋም የተበደሩት ብድር ካለ ከፍለው ያጠናቀቁ ወይም በአግባቡ እየከፈሉ ያሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ እንዲሁም በብድር ዘመናቸው ከሚያገኙት ገቢ ላይ በፋይናንስ ተቋማት የቁጠባ ባህል ያላቸው፤

- ነባር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሆነው የሂሳብ መዝገብ ያላቸውና የሂሳብ መዝገባቸውን ያስመረመሩ አዲስ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከሆኑ የሂሳብ መዝገብ እንዲያዘጋጁ ድጋፍ በማድረግ በቀጣይም ሂሳባቸውን ለማስመርመር ፍቃደኛ የሚሆኑ መሆን ይገባቸዋል፡፡
- ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ከሆኑ ዓመታዊ ሂሳባቸውን ያስመረመሩና የተከታታይ ሁለት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች በታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ደረጃ ያሉ እንደ አስፈላጊነቱ ከሚመለከተው አካል የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጡ መሆን ይገባቸዋል፡፡
- የዱቤ ግዢ ኪራይ አገልግሎት ጥያቄዎች የዕድገት ደረጃቸው በጥቃቅን ጀማሪ፤ታዳጊና የበቃ እንዲሁም በአነስተኛ ጀማሪና ታዳጊ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ መቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ለሚቀርብላቸው የካፒታል እቃ የመድህን ሽፋንና ዕድሳት ወጪን ለመክፈል ፈቃደኛ የሆኑና መተማመኛ የሰጡ፡፡
- የስራ ማስኬጃ ብድር ፈላጊዎች የሥራ ማስኬጃ ብድሩን ከፋይናንስ ተቋማት ስለማግኘታቸው ወይም በራሳቸው ገንዘብ መስራት የሚያስችላቸው አቅም እንዳላቸው ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችሉ፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ለማግኘት የሚፈልጉ ተጠቃሚዎች በንግድ ህጉ መሠረት ህጋዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ (የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ፣ የመተዳደሪያ ደንብና የመመስረቻ ጽሑፍ) ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ግብር የመክፈል ግዴታ ያለባቸው ከሆኑ ግዴታቸውን መወጣታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
- ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ፣ የመስራት አቅምና ችሎታ ያላቸው፤
- ከሚኖሩበት ቀበሌ የነዋሪነት ማረጋገጫ ማሰረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤

ከላይ የተዘረዘትን መስፈርቶች ካሟሉ በኋላ የሚከተሉት አከላት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል

- ሴቶች እና ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ፤
- የዩኒቨርሲቲና የቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎች፤

- ሁሉም የማህበሩ አባላት ወይም የተወሰኑት አባላት በሚሰማሩበት የስራ ዘርፍ ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትስልጠና የወሰዱ እና ከምዘና ማዕከላት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያላቸው፤

ከላይ የተገለጹትን መስፈርቶች መሠረት በማድረግ ኢንተርፕራይዞችን የመመልመል ኃላፊነት በስትራቴጂው ላይ እንደተገለጸው ፈጻሚ አካላት የሆኑት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ/ቢሮ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ/ቢሮ፣ የሴቶች ወጣቶችና ሕጻናት ቢሮ፣ አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት እና የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ኢ.ማ ናቸው፡፡

## 3.6. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ስልጠና

ተጠቃሚዎች ከአገልግሎቱ በፊትም ሆነ በኋላ ስለመሳሪያው አጠቃቀምና አያያዝ፣ ስለኪራይ አከፋፈል ሁኔታ ስለ ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም እና የቁጠባ ጠቀሜታና የአሰራር ሁኔታ ስልጠና ሊያገኙ ይገባል፡፡ የሚሰጡት ስልጠናዎች በዋናነትም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የንግድ ዕቅድ አዋጭነት
- የቁጠባ ጠቀሜታዎች፣
- የሂሣብ መዝገብ አያያዝና አጠቃቀም ፣
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥና ሂደቱን፤
- የአገልግልት ክፍያ ምጣኔውንና የአከፋፈል ሥርዓቱን፣
- የካፒታል ዕቃ የመድህን አሸፋፈን ሂደቱን፣
- የቅድመ ክፍያ እና ስለኪራይ አከፋፈል ስርዓት፣ በተመለከተ በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አክስዮን ማህበሩ ስልጠናውን ይሰጣል፡፡

## 3.7. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት

### 3.7.1. የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ማመልከቻ ስለ ማቅረብ

የካፒታል ዕቃ ኪራይ ጥያቄ ማመልከቻ መሰረታዊ የሆኑ ተከራዩ ሊስራው ያሰበውን ስራ ሁኔታ የሚገልጽ ሆኖ በየትኛው ዓይነት/ሞዳሊቲ/ እና መቼ የካፒታል ዕቃውን ማግኘት እንደፈለገ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ማመልከቻ ፎርሙ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች መያዝ ይገባዋል፡-

- የተከራዩን የግል ሁኔታ፣ /ፆታ፣ ዕድሜ፣ የት/ደረጃ፣ ያገባ/ያላገባ ወዘተ/፣
- የተከራዩን አድራሻና የስራ ቦታው፣
- የተከራዩን የቢዝነስ ሁኔታና የምርት ሂደቱን፣
- የሚያሰማራቸው የሰራተኞች ብዛት፣
- የመሳሪያውን ዝርዝር መግለጫና የአቅራቢዎቹ መግለጫ፣
- የመሳሪያው የስራ ሁኔታና የአጠቃቀም ሁኔታ ፣
- ተከራዩ ያለው ሃብት ዝርዝር፡- ቤት መኪና መሳሪያዎችና ሌሎች፣
- በኪራይ ዘመን ከቢዝነሱ የሚጠበቅ ገቢ ከሚያመርተው የምርት መጠን ጋር፣
- የገበያ ሁኔታውን የሚገልጽ፣
- በኪራይ ዘመኑ ከሌሎች ገቢ የሚገኝ ገቢ መጠን ፣
- በኪራይ ዘመኑ ለቢዝነሱ ስለሚኖር አጠቃላይ ወጪ፣
- በኪራይ ዘመኑ ከቢዝነሱ ውጭ ስለሚኖር አጠቃላይ ወጪ፣
- የኪራይ ዓይነቱ /የፋይናንስ ሊዝ ወይም የዱቤ ግዥ/፣
- የአመልካቹ ፊርማ ፣

## 3.7.2. የአዋጭነት ግምገማ ስለ ማካሄድ

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት የቀረበው ቢዝንስ ፕላን በዋናነት የአዋጭነት ግምገማ በአክስዮን ማህበሩ የሚደረግ ሆኖ የሥራ ማስኬጃ ብድርን የሚያጠቃልል ከሆነ በአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ግምገማው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ በዚህ ግምገማ ወቅት የሚታዩ ዋና ዋና ነጥቦች፡-

- የንግድ ሥራ ዕቅድ ዝግጅቱ
- የካፒታል ዕቃው የሚተከልበትና የሚሰራበት የሥራ ቦታ ህጋዊ መሆኑ ማረጋገጥ፣
- የካፒታል ዕቃው የሚተከልበት ቦታ የባለቤትነት ሁኔታ ማረጋገጥ/ ጊዜያዊ/ ቋሚ/ ኪራይ፣
- በአካባቢው ያሉት ተወዳዳሪዎች ሁኔታ ማወቅ፣
- ቢዝነሱ አስተማማኝ አቅርቦት መኖሩን፣
- የወቅቱ የገበያ ሁኔታ፤

- በካፒታል ዕቃው  የሚቀርበው የአገልግሎት፣ የምርትና የንግድ አሰጣጥ ሁኔታ፣ ገበያውም ዘላቂ መሆኑን፣
- ቢዝነሱ የሚያስገባው ገቢና ወጪ ሁኔታ፣
- የቢዝነሱ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት፣
- በቂ የመለዋወጫ ዕቃና አክሰሰሪስ የጥገና አገልግሎት መኖር፤
- ኢንተርፕራይዙ ዘመናዊ የሥራ አመራር፤ የክህሎትና የብቃት ልምድ፣
- ቢዝነሱ የሚፈጥረው የስራ እድልና ለህብረተሰቡ የሚሰጠው ማሕበራዊ ጠቀሜታ፤
- የአከባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ይከናወናል

ከላይ በተገለጸው መሠረት በአንድ ማዕከል ደረጃ ባለው /የአክስዮን ማህበሩ ባለሙያ የኢንተርፕራይዙ ዓይነት፣ ለዘርፉ በተሰጠው ትርጉምና በተሰማራበት የሥራ ዘርፍ ለይቶ ለአክስዮን ማህበሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

- ከፍ ሲል በተገለጸው አግባብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን ማዕቀፍ የሆነውን የካፒታል ዕቃ ገንዘብ መጠን ይወስናል፡፡
- ከቅ/ጽ/ቤቱ የመወሰን ስልጣን በላይ ከሆነ ለዋናው መ/ቤት መነሻ የውሳኔ ሃሳቡን በመሰጠት ያስተላልፋል ዋናው መስሪያ ቤት ገምግሞ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

የካፒታል ዕቃ መግዣ ገንዘብ መጠኑ የመወሰን ስልጣን ደረጃን በተመለከተ አክስዮን ማህበራቱ እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያስቀምጡት ይሆናል፡፡

### 3.7.3. የካፒታል ዕቃ ግዢ ቅድመ ሁኔታዎች

ተከራይ የሚፈልገውን የካፒታል ዕቃ ዝርዝር መግለጫ /specification/ ለአከራይ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በቀረበው ዝርዝር መግለጫ መነሻነት አከራዩ /ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ዓይነትና የሚገኝበትን ቦታ የሚገልጽ ማወዳደሪያ ከአቅራቢዎች ያሰባስባል፡፡ በአቅራቢዎች የማወዳደሪያ ቅጽ ላይ አክስዮን ማህበሩ በግዢ መመሪያው ውስጥ ያስቀመጣቸው መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ቢያንስ የሚከተሉትን ጉዳዮች በግልጽ መዘርዘር ይኖርበታል፡-

- የካፒታል ዕቃው ዝርዝር መግለጫ /specification/፣ ዋጋንና የአከፋፈል ሁኔታን፤

- በምን ያህል ጊዜ ማቅረብ እንደሚችልና ማወዳደሪያው የሚቆይበትን ጊዜ
- የካፒታል ዕቃው  ዝርዝር ሁኔታና ቴክኒካል ባህርያቱን ከእነ መለዋወጫና አከሰሰሪስ ይዞቱ
- የካፒታል ዕቃው ርክክብ ስርአቱንና ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ የት እንደሚያደርስ
- የተከላ፣ የሙከራና የአጠቃቀም ስልጠና ሁኔታ
- የዋስትና ሁኔታን /warranty /
- ከግዢ በኋላ ስለሚኖር አገልግሎትና የጥገና ስምምነት

ከላይ በተገለጸው አግባብ ማወዳደሪያው ከተሰበሰበ በኋላ በአክሲዮን ማህበሩ የግዥ መመሪያና ማኑዋል መሠረት፣ ግዢው ይፈጸማል፡፡

### 3.7.4. የካፒታል ዕቃ ዓይነት እና አቅራቢ ድርጅት ስለ መለየት

የካፒታል ዕቃ አቅራቢዎች ሦስት ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

### ሀ/ በሀገር ውስጥ ዕቃዎችን የሚያመርቱ አቅራቢዎች

- በሀገር ውስጥ በብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን እና በሌሎች አምራችና አቅራቢዎች የሚመረቱና የሚቀርቡ የካፒታል ዕቃዎችን በመለየት እንዲመረት/እንዲቀርብ የማድረግ፤
- በየአካባቢው በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ድጋፍ የካፒታል ዕቃ የማምረት ብቃታቸው የተረጋገጠላቸው አብዢ ኢንተርፕራይዞች የተከራዮችን ፍላጎት መሠረት ያደረገ አቅርቦት እንዲኖር ይደረጋል፤

### ለ/ አስመጪ አቅራቢዎች

በሀገር ውስጥ የማይመረቱ ሆነው በኢንተርፕራይዞቹ ፍላጎት መሠረት በማድረግ በአስመጪ አቅራቢዎች የሚቀርቡ የካፒታል ዕቃን በግዢ መመሪያ መሠረት በመጋበዝ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

### ሐ/ የውጭ አገር አቅራቢ/አምራች

በሀገር ውስጥ የማይመረቱና መገኘት የማይችሉ መሆኑ በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ የካፒታል ዕቃዎችን ህጋዊ ፍቃድ ያላቸውን እና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያላቸውን ተቋማት በግዥ መመሪያው መሠረት በመጋበዝ የካፒታል ዕቃን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

በዚህ ደረጃ ተከራይ የመሳሪያ ዓይነት የመምረጥና አቅራቢዎችን የመለየት ተግባር ቀድሞ ማዘጋጀትና መለየት ይጠበቅበታል፡፡ ይሁንና የካፒታል ዕቃን ጥራትና ብቃት ለቢዝነሱ ቀጣይነት መረጋገጥ እንደ ዋስትናም ጭምር የሚያገለግል በመሆኑ፤ በተለይ የመሳሪያ ዓይነቱን የመለየትና ደረጃውን የመምረጥ ለተከራይ የመወሰን መብት የሚሰጠው ሲሆን የአቅራቢን የመለየት ተግባር ግን በአክስዮን ማህበሩ የግዢ ስርአት መሰረት ሆኖ በጋራ የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የሥራው ባህሪይ አዲስ እንደመሆኑ መጠን በፌደራል ደረጃ የዝርዝር መግለጫ እና የግዢውን ሂደት ላይ የቴክኒክ ምክር አገልግሎት የሚሰጥ አለም አቅፍ አማካሪ ድርጅት / ሱፐርቫይዘር/ የሚቀጠር ይሆናል፡፡

### 3.7.5. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ የብድር ዋስትና ፈንድ በተመለከተ

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጨማሪ ንብረት ወይም መያዣ የሚያስፈልገው ባይሆንም የኪራይ ክፍያ ቢበላሽ ቀደም ሲል በየክልሉ በተቋቋመው የብድር ዋስትና ፈንድ አሰራር የሚሸፈን ሆኖ የካፒታል ዕቃ ለሌሎች ኢንተርፕራይዝ በኪራይ/በሽያጭ/ በሚተላለፍበት ወቅት ቀደም ሲል ከፈንዱ ወጪ የሆነውን ገንዘብ ተመላሽ ይሆናል፡፡

### 3.7.6. የመሳሪያ ኪራይ ውል ስምምነት ስለ ማድረግ

ቢዝነሱና የመሳሪያው ዓይነት ተገምግሞ ከጸደቀ በኋላ ተከራይና አከራይ የመሳሪያ ኪራይ ውል ስምምነት ያደርጋሉ፡፡ የውል ስምምነቱ ሰነድ በአክስዮን ማህበሩ የሚዘጋጅ ሲሆን በዋናነት በመሳሪያ ግዢ መወዳደሪያ ላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር ሁኔታዎች ያካተተ መሆን ይገባዋል፡፡

### 3.7.7. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኪራይ አወሳሰን ሥርዓት

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ኪራይ የማሰባሰብ ተግባር በወቅቱና በውሉ መሰረት መከናወን የሚገባው ሲሆን የአከፋፈል ስርአቱ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

❖ የኪራይ ክፍያ ጊዜ፡

- የክፍያ ጊዜን በተመለከተ ከፍተኛው የክፍያ ጊዜ ጣሪያ በቀጣይ በብሔራዊ ባንክ የሚወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደየሥራው ዓይነት፣ የመመለስ አቅም እና የካፒታል ዕቃው የአገልግሎት ዘመን ይዘት ከፍተኛው የመክፈያ ጊዜ እስከ ስድስት ዓመት ይሆናል፡፡
- የኪራይ ክፍያ ሥርዓቱ በተወሰነ ጊዜያት ወይም በየወሩ ወይም በየሦስት ወሩ የሚፈጸም ሆኖ እንደ ሥራው ባህሪ በየስድስት ወሩ የአከፋፈል ሥርዓት ይኖራል፡፡

❖ ወለድ፡

- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ለሚከራዩት ዕቃ ወለድ እንዲከፍሉ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የወለድ መጠን እንደየ ክልሉ የሚወሰን ሆኖ ከፍተኛ የወለድ መጠን ከ12 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡ በቀሪ ሚዛን ላይ የሚሰላ /Declining Balance/ ይሆናል፡፡
- የአገልግሎት ክፍያየካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚዎች ለሚሰጣቸው የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አይጠበቅባቸውም፡፡
- ተከራዩ ወለድ /ኪራይ መሰላት የሚጀምረው መሳሪያው ኮሚሽን ከተደረገና ውል ከተያዘ ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፤

❖ የእፎይታ ጊዜ

የእፎይታ ጊዜ እንደየ ኢንተርፕራይቱ ዓይነትእና እንደሚያመርቷቸው ምርቶች የሚለያይ ሆኖ ከፍተኛው ጊዜ 6 ወር ይሆናል፡-

| የኢንተርፕራይዙ ዓይነት | ማኑፋክቸሪንግ |
|---|---|
| አዲስ ኢንተርፕራይዝ | ከኮሚሽኒንግ በኋላ እስከ ስድስት ወር |
| ለነባር ኢንተርፕራይዝ | ከኮሚሽኒንግ በኋላ እስከ አራት |

| | |
|---|---|
| | ወር |
| | ከተሰጠው የእፎይታ ጊዜ አስቀድሞ ክፍያ መጀመር ይቻላል፡፡ |

### 3.7.8. የካፒታል ዕቃ ግዢ ስለ ማከናወን

ተከራይ ቅድመ ክፍያ ማስቀመጡ ከተረጋገጠ በኋላ በተዘጋጀውና ተከራይና አከራይ በተስማሙበት ስፔስፊኬሽን መሰረት ለአቅራቢው የግዢ ወይም የስራ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ በዚህ ወቅት የካፒታል ዕቃው የሚያስረክብበት ቦታ በግልጽ መገለጽ ይኖርበታል፡፡ ስለ ካፒታል ዕቃው ደህንነት ዋስትና ጉዳይና ከግዢ በኋላ ያሉ አገልግሎቶችና ጥገና ስራዎች በአቅራቢውና በአከራይ በጋራ በሚገባው ውል መሠረት ይተገበራል፡፡

በግዢ የሥራ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት፡-

- ለሥራው አስፈላጊ የሆነውን የካፒታል ዕቃ የመምረጥ በዋነኛነት በተከራይ ሆኖ በጋራ ከኩባንያው ጋር የሚከናወን ሲሆን አቅራቢውን የመለየት ተግባር የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አክስዮን ማህበር ይሆናል፡፡
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተከራይ የራሱን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የካፒታል ዕቃውንና የካፒታል ዕቃ አቅራቢ በነፃነት የመምረጥ መብት ቢሰጠውም አክስዮን ማህበሩ ለኪራይ የሚውለው የካፒታል ዕቃ ለቢዝነሱ ጥራትና ቀጣይነት እንደ ዋስትና ስለሚያገለግል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስፔሲፊኬሽን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡
- አቅራቢዎችና አምራች ድርጅቶች በአክስዮን ማህበሩ በኩል በቀረበላቸው ስፔስፊኬሽን መሰረት የካፒታል ዕቃ እሰከነ መለዋወጫ ዕቃዎቹ መዘጋጀቱን እንዲሁም የተከላና የሙከራ ጊዜ ከአክስዮን ማህበሩ ጋር በተደረገው ስምምነት መሰረት የሚያከናውኑ መሆን አለባቸው::
- አቅራቢዎች መልካም ስም ያላቸውና በቂ የዋስትና ጊዜ የሚሰጡና ቀና ትብብር ለማድረግ ዝግጁ የሆኑ እና በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፡፡
- ተከራዩ ቅድመ ክፊያ ከከፈለ በኋላ የካፒታል ዕቃውን ለመረከብ የሚወስደው ጊዜ ከ6 ወራት መብለጥ የለበትም፡፡

የካፒታል ዕቃ መግዣ መጠን፡- ለአንድ ተጠቃሚ የሚገዛው የካፒታል ዕቃዎች አጠቃላይ መግዣ ዋጋ ዝቅተኛው መጠን ከብር 50,000 ማነስ የለበትም፡፡ ከፍተኛው ጣሪያን በተመለከተ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በታች ዋጋ ላላቸው የካፒታል ዕቃዎች ግዢ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በሚሰጡት የብድር አገልግሎት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## 3.7.9. መሳሪያ ማጓጓዝና ምዝገባ ስለ ማከናወን

ሀ/ መሳሪያ ማጓጓዝ

የመሳሪያ ርክክብ ስርአቱ በተቻለ መጠን የተከራይ የስራ ቦታ ላይ እንዲሆን የሚደረግ ሲሆን አቅራቢ በራሱ ማጓጓዣ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግን የተከራይ የስራ ቦታ ዝግጅት ያልተጠናቀቀ ከሆነና በተከራይና አከራይ ስምምነት አክስዮን ማህበሩ በሚያዘጋጀው መጋዘን እንዲቀመጥና ርክክብ እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

ይህም ተግባር የሚከናወነው በሁለት አግባብ ሲሆን

- አንደኛው አቅራቢው በተከራይ ቦታ ሲያስረክብ
- ሁለተኛው በማከማቻ መጋዘን ርክክብ ሲፈጸም መከናወን ይኖርበታል፡፡

በርክክብ ወቅት

- የካፒታል ዕቃ በስፔስፊኬሽን መስረት መሆኑን፣
- መለያ ቁጥሩ ትክክል መሆኑን፣
- አክሰሰሪና መለዋወጫ መኖራቸውን አክስዮን ማህበሩ በማረጋገጥ ርክክብ ይካሄዳል::

ርክክቡ በተቻለ መጠን ተከራይ በሚያዘጋጀው የስራ ቦታ ላይ አቅራቢው እንዲያስረክብ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግን በተለያዩ ምክንያቶች የተከራይ ቦታ ዝግጅት ወደ ኋላ የዘገየ ከሆነ አክስዮን ማህበሩ በሚያዘጋጀው ቦታ የተከራይ ሙሉ ስምምነት ባለበት ሁኔታ ማስረከብ ይቻላል፡፡ የመረካከቢያው ሰነድ ሲፈረም የተከራይ ኢንተርፕራይዝ ባለቤት ወይም ሕጋዊ ውክልና ያለው የማህበሩ አባል መቅረብ አለበት::በየትኛውም መንገድ ርክክቡ ሲፈረም

የኢንተርፕራይዙ ተጠሪ እንጂ ተቀጣሪ ሰራተኛ ሊሆን አይገባም:: የመረካከብያው ቃለጉባዔ ሰነድ ደግሞ የውሉ አካል ሆኖ እንዲያያዝ ይደረጋል::

ለ/ የካፒታል ዕቃ ምዝገባ

በኪራይ የሚሰጡት የካፒታል ዕቃዎች አክስዮን ማህበር ስም የሚገዙ ሆኖ ሕጋዊ የአክስዮን ማህበሩ አርማ እና በምዝገባ ወቅት የተሰጠው መለያ ቁጥር እንዲኖረው ተደርጎና ስልጣን በተሰጠው አካል መመዝገቡን በማረጋገጥ ርክክብ እንዲፈፀም ይደረጋል::

የካፒታል ዕቃ ምዝገባ የሚከናወነው መሳሪያው እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ እንዲሁም ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የማድረግ ተግባር ነው፡፡ ምዝገባውም በየደረጃው ስልጣን በተሰጠው አካል የሚከናወን ይሆናል:: የካፒታል ዕቃው ያለመዝጋቢው አካል እና ያለአክስዮን ማህበሩ ዕውቅና ከቦታ ወደ ቦታ ማዘዋወር አይቻልም፡፡

### 3.7.10. ኢንሹራንስ መግባት፣ የውል ምዝገባ ስለ ማከናወን እና ስለ ማስተላለፍ

የካፒታል ዕቃው በአዋጅ ቁጥር 103/1990 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1(መ) እና 3(ሐ) መሰረት ኢንሹራንስ እንዲገባለት ይደረጋል፡፡ በዚሁ መሰረት የኢንሹራንስ ወጪው በተከራይ የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ይህ ተግባር የሚከናወነው በርክክብ ወቅት አክስዮን ማህበሩ በጋራ ከሚሰራው የኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር ይሆናል፡፡ ለማምረቻ መሳሪያዎች  የሚገባው ኢንሹራንስ አይነት የእሳት አደጋ ሲሆን ለኮንስትራክሽን አገልግሎት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎች አጠቃላይ የኢንሹራንስ ሽፋን እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

አከፋፈሉን በተመለከተ የመጀመሪያውን ክፍያ አክሲዮን ማህበሩ የሚከፍል ሲሆን የቀሪዎቹን ዓመታት ተከራዩ በየወሩ በብድርና ቁጠባ ተቋማት በመቆጠብ በየዓመቱ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዝ ይህን ካላደረገ አከራዩ ክፍያውን በመክፈል የኪራይ ዋጋው ላይ በማሰብ የሚያስከፍል ይሆናል፡፡

### 3.7.11. የካፒታል ዕቃ ተከላና ሙከራ ስለ ማከናወን

የካፒታል ዕቃ ለተጠቃሚዎች ከመተላለፉ በፊት ተከላና የሙከራ ምርት በአቅራቢው ድርጅት በኩል መከናወኑን በአከራዩ እና በአማካሪ ድርጅት/በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት/ የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡

### 3.7.12. የካፒታል ዕቃ አጠቃቀም ሥልጠና መስጠት፣ ጥገናና ዕድሳት ስለ ማድረግ

ሀ/ የካፒታል ዕቃ አጠቃቀም

- የካፒታል ዕቃ ኪራይ ውል መሰረት ንብረቱን የሚጠቀምበት ተከራዩ በመሆኑ የካፒታል ዕቃ በጥንቃቄ ይዞ የመጠቀም ፣ተከታታይ ጥገናና እድሳት ማድረግ አለበት:: ይህንን ደንበኛው (ተካራዩ) አውቆትና ተረድቶት በኪራዩ ውል ውስጥ ተካቶ ደንበኛው እንዲፈርም ይደረጋል::
- የካፒታል ዕቃ አቅራቢው በውሉ መሰረት ስለ ካፒታል ዕቃ አጠቃቀምና ጥገና ስልጠና እንዲሰጥ ይጠበቅበታል፡፡
- ተከራይ በዱቤ ግዢ የተከራየውን የካፒታል ዕቃ በተተከለበት ቦታ(ሳያንቀሳቅስ) ለሌሎች ኢንተርፕራይዞች በአጭር ጊዜ ኪራይ አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡

ለ/ የካፒታል ዕቃ ጥገናና እድሳት

- ጥገናና እድሳት በሚደረግበት ወቅት ከአክስዮን ማህበሩ እውቅና ውጪ ከቦታ ወደ ቦታ ማንቀሳቀስ ፈጽሞ አይፈቀድም::
- የጋራንቲ ጊዜ ከአበቃ በኋላ ለሚደርሱ ብልሽቶች ለጥገናና ዕድሳት የሚወጣውን ወጪ በተከራዩ የሚሸፈን ይሆናል ይህም በውሉ ላይ በግልጽ ተካቶ ደንበኛው እንዲፈርም ይደረጋል፡፡
- የጥገናና እድሳት ደረጃው ቀላል ከሆነ ተከራዩ ጥገናና እድሳት የሚደረግበትን ቦታ፣ለጥገናና እድሳቱ የጠየቀው ወጪና በየትኛው ቦታ(ጋራዥ) ጥገናና እድሳት እንደሚደረግለት ለአክስዮን ማህበሩ በወቅቱ ማሳወቅ አለበት:: ከዚያ በኋላ አክስዮን ማህበሩ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

- ከባድ የሆነ ጥገናና ዕድሳት በተመለከተ በአክስዮን ማህበሩ እና ኢንተርፕራይዙ በጋራ በሚመርጡት ቦታ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡
- የጥገናና ዕድሳቱ በአራት አማራጮች መከናወን ይችላል፡፡

**በአቅራቢ ተቋማት፡-**

- ለካፒታል ዕቃ የጋራንቲ ጊዜ ከማለቁ በፊት ለሚያጋጥሙ ብልሽቶች አቅራቢው የመጠገን ኃላፊነት አለበት፡፡ የጋራንቲው ጊዜ ካለቀ በኋላ ለሚከሰቱ ብልሽቶች ከአቅራቢው ጋር በሚደረግ ስምምነት መሰረት የጥገናና ዕድሳት የሚከናወን ይሆናል፡፡

**በኢንተርፕራይዞቹ አባላት፡-**

- ከኢንተርፕራይዞቹ አባላት መካከል ስለመሳሪያው ጥገናና ዕድሳት ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ የጥገናና ዕድሳት ስራውን እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ ሥልጠናው በአቅራቢ ተቋማት ወይም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

***የጥገናና ዕድሳት ስራ ኢንተርፕራይዞች በማደራጀት፡-***

- ለጥገናና ዕድሳት ኢንተርፕራይዞች የሚሆን በቂ ሥራ መኖሩ ሲረጋገጥ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ /ቢሮ/ አማካኝነት ኢንተርፕራይዞች እንዲደራጁ በማድረግ የካፒታል ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጎ የጥገናና ዕድሳት ስራውን እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

***የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት በሚያቋቁሙት የጥገናና ዕድሳት ክፍል***

የካፒታል ዕቃዎች ከጋራንቲ ጊዜ በኋላ ለሚደርሱ ብልሽቶች ጥገናና ዕድሳት አገልግሎት የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የጥገና ክፍል በማደራጀት በተመጣጣኝ ክፍያ የጥገናና ዕድሳት አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

### 3.7.13. ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ስለ ማከናወን

አክስዮን ማህበሩ የካፒታል ዕቃው ካከራየ በኋላ ባሉት 15 ቀናት ጊዜ ውስጥ የካፒታል ዕቃው ስራ መጀመሩንና ለሚፈለገው ስራ መዋሉን ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቋሚ ፕሮግራም ወጥቶለት በፈፃሚ አካላት በየወሩና በየሶስት ወሩ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡

በክትትል ወቅት በዝርዝር መታየት ያለባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች

- የካፒታል ዕቃው እየሰራ መሆኑን፣
- በካፒታል ዕቃው ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ካሉ፡- በአምራች ኩባንያው ወይም በስራ ወቅት የተፈጠረ ችግር መሆኑን
- የካፒታል ዕቃው ለታለመለት ዓላማ መዋሉን፣
- የካፒታል ዕቃው ለሶስተኛ ወገን አለመተላለፉንና በተከራዩ ስራ ቦታ ላይ መዋሉን፣
- ህጋዊ የሆኑ ሁኔታዎች መሟላታቸውን የንግድ ፈቃድ መታደስ፣ የግብር ክፍያ በወቅቱ መከናወኑንና ሌሎች ህጋዊ ሁኔታዎችን፣
- የኢንሹራንስ ፕሪሚየም በወቅቱ መከፈሉን
- በአክስዮን ማኅበሩ የተሰጠው መለያ ቁጥር/ታግ/ በቦታው ላይ መኖሩን
- የካፒታል ዕቃው ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች መኖር አለመኖራቸውን፣

### 3.7.14. የካፒታል ዕቃ ባለቤትነትን ስለ ማስተላለፍ

የዱቤ ግዢ ኪራይ በሚሆንበት ወቅት ተከራዩ ክፍያ በፈጸመ መጠን የካፒታል ዕቃው ባለቤትነት መብት ያለው ሲሆን ሙሉ በሙሉ ባለቤትነቱ የሚሰጠው የመጨረሻውን ክፍያ ባጠናቀቀበት ወቅት የሚተላለፍለት ይሆናል፡፡ ክፍያውን ስለማጠናቀቁ እና የካፒታል ዕቃው ባለቤት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት በአክስዮን ማህበሩ ይሰጠዋል፡፡ የፋይናንሻል ሊዚንግ በሚሆንበት ወቅት እስከ መጨረሻው ክፍያ ድረስ ባለቤትነቱ የአክስዮን ማህበሩ ሆኖ የኪራይ ክፍያው ሲጠናቀቅ ባለቤትነትን የማስተላለፍ ተግባር በአከራይና በተከራይ መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ፡፡

### 3.7.15. ውል የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎችና ቀጣይ የሚወሰዱ እርምጃዎች

የካፒታል ዕቃው ስምምነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል

- በአከራይና ተከራይ ተስማምተው የስምምነት ውሉ ሲያቋርጡ፣

- በተከራይ ፍላጎት የኪራይ ስምምነቱ ሊቋረጥ ይችላል በዚህ ወቅት ተከራይ ከስምምነት መቋረጥ በፊት የነበሩ ወጪዎችንና የጉዳት ካሳ መክፍል ግዴታ ይኖርበታል፡፡
- ተከራይ በገባው ውል መሰረት የካፒታል ዕቃውን ለታለመለት ዓላማ ሳያውል ከቀረ አከራይ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስምምነቱ መቋረጥ ይችላል በዚህ ወቅትም ተከራይ ከስምምነት መቋረጥ በፊት የነበሩ ወጪዎችንና፣ የጉዳት ካሳ መክፍል ግዴታ ይኖርበታል፡፡
- ተከራዩ የካፒታል ዕቃው በተላለፈለት ወቅት አገልግሎቱን የሚቀንስ ጉድለት ያለበት ሆኖ ካገኘው ስምምነቱን አቋርጦ የካፒታል ዕቃውን የመመለስ መብት ያለው መሆኑ በውሉ ላይ መገለጽ ይኖርበታል፡፡
- የውል ስምምነቱ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሲቋረጥ ወይም በፋይናንስ ኪራይ መሠረት የውል ጊዜው ተጠናቆ የተመለሱ የካፒታል ዕቃዎችን አክስዮን ማህበሩ ለሌላ ተከራይ መልሶ ማከራየት ወይም መሸጥ ይችላል፡፡
- አከራይ በገባው ውል መሠረት የካፒታል ዕቃውን ማቅረብ ካልቻለ ከስምምነት መቋረጥ በፊት ተከራዩ ለከፈለው ቅድመ ክፍያ ወለድ በማሰብ በተጨማሪ የካፒታል ዕቃውን ዋጋ 5 በመቶ የጉዳት ካሳ ለተከራይ ይከፍላል፡፡

### 3.7.16. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኪራይ አመላለስ ምጣኔ እና የተቋማቱ ቀጣይነት / Repayment rate & Sustainablity/

- ያለውን የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነት ችግር ለመቅረፍና ተደራሽነትን ይበልጥ ለማሳደግ ሁሉም ፈፃሚ እና ባለ ድርሻ አካላት ለካፒታል ዕቃ ክፍያ ማስመለስ ሥራ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል::
- በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ጽ/ቤት ወይም ቅ/ጽ/ቤት አማካይነት በየሦስት ወሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ኪራይ ክፍያ አመላላስ ምጣኔ አፈጻጸም ሪፖርት ቀርቦ ከተገመገመ በኋላ የአክስዮን ማህበሩ የገንዘብ አስተዳደር ጤናማ ለማድረግ የኪራይ ክፍያ አመላለስ ምጣኔ ከ97% በታች እንዳይሆን ሁሉም ፈፃሚና ባለድርሻ አካላት በጋራ ተረባርበው ኪራዩን እንዲከፈል ያደርጋሉ::

- ተጠቃሚዎች የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት የኪራይ ክፍያቸውን በመመለሻ ቀናቸው ካልመለሱ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ ጽ/ቤት በቀበሌ ደረጃ ካለው ኮሚቴ ጋር በመሆን የተፈጠረውን ውዝፍ እንዲመለስ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ፡፡ ውዝፉ በዚህ ኮሚቴ የጋራ ጥረት በ7 ቀናት ውስጥ ካልተመለሰ የእያንዳንዱ ደንበኛ ዝርዝር፣ የውዝፍን መጠንና ምክንያት ያካተተ ሪፖርት በ5 ቀናት ውስጥ ለከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ያሳውቃሉ፡፡
- የከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት በሪፖርቱ መሰረት ደንበኞች ውዝፍ ከፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ደንበኛውን በማወያየት በ30 ቀናት ውስጥ እንዲመልሱ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ውዝፉ እንዲመለስ ያደርጋል፡፡
- ከላይ በተቀመጠው አግባብ የኪራይ ክፍያውን በወቅቱ ያልከፈሉ ኢንተርፕራይዞችን ማምረቻ መሳሪያ በእጃቸው እስከቆየበት ጊዜ ያለው ክፍያ ታስቦ እንዲከፍሉ በማድረግ በአቅራቢ ተቋሙ የቀረበላቸውን የማምረቻ መሳሪያ እንዲመልሱ ይደረጋል፡፡
- ከላይ በተቀመጠው አግባብ በ90 ቀናት ውስጥ ተጠቃሎ የማይመለስ ከሆነ ውዝፉን ከነወለዱ ከዋስትና ፈንዱ ገንዘብ እንዲተካ ይደረጋል፡፡ ከብድር ዋስትና ፈንዱ ውዝፉ ለአቅራቢው ተቋም ከተተካ በኋላ ከተጠቃሚዎቹ የሚመለሰው የኪራይ ክፍያ ወደ ዋስትና ፈንዱ የተቀማጭ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፡፡

### 3.7.17. የመጋዘን አስተዳደር ሥርዓት / Store Management/

አክስዮን ማህበሩ የካፒታል ዕቃዎችን በመግዛት ለኢንተርፕራይዞች የማስተላለፍ ተግባር የሚያከናውን በመሆኑ የመጋዘን አገልግሎት ተግባር የሚያከናውንበት አስገዳጅ ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ በተቻለ መጠን ካፒታል ዕቃዎች ቀጥታ ከአቅራቢ ለኢንተርፕራይዞች መተላለፍ ያለበት ስርአት መከተል በዋንኛነት የሚተገበር ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን አሰገዳጅ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ወቅት የካፒታል ዕቃዎች በመጋዘን በአግባቡ ሊጠበቁና ሊያዙ ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት የመጋዘን ቦታ የሚሆን በክልል መስተዳድሮችና የከተማ አስተዳደሮች ለአክስዮን ማህበሩ ማዘጋጀት

የሚገባቸው ሲሆን አክስዮን ማህበሩም መጋዘኑን የሚያስተዳድርበትን አሰራር ሥርዓት መዘርጋትና የሰው ሃይል የመመደብ ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡

የመጋዘን አገልግሎቱ አዲስ ለሚገዙ የካፒታል ዕቃዎች አስገዳጅ ሁኔታዎች ካልተፈጠሩ በስተቀር መጠቀም አስፈላጊ አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል ተከራዮች በአግባቡ ያልተጠቀሙባቸውን የካፒታል ዕቃዎች መልሦ ለመጠቀም በዋናናት የሚያገለግል ይሆናል፡፡ በዚህም ወቅት በተቻለ መጠን ተከራዮች የካፒታል ዕቃውን ለመጠቀም የማያስችላቸው ሁኔታ ሲፈጠር ችግራቸውን ለይቶ የክፍያ ጊዜያቸው እንዲራዘም በማድረግ የካፒታል ዕቃውን የሚጠቀሙበት ሁኔታን መፍጠር የመጀመሪያ አማራጭ ሲሆን በሁለተኛ አማራጭ የካፒታል ዕቃውን ባለበት ቦታ ለሌላ ኢንተርፕራይዝ ማስተላለፍ ይሆናል፡፡ እነዚህ ሁለት አማራጮች መፍትሄ የማይሆኑ ከሆነ የካፒታል ዕቃውን ከቦታው በማንሳት በመጋዘን ማስቀመጥ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተመዝግቦ የነበረው የውል ስምምነት እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

ወደ መጋዘን የሚገቡም ሆነ ለተከራይ የሚተላለፉ የካፒታል ዕቃዎች በአግባቡ በንብረት ገቢና ወጪ መዝገብ መመዝገብ ይኖረባቸዋል፡፡ የገቢና ወጪ መዝገቡ የካፒታል ዕቃውን ዝርዝር መግለጫ ማለትም ርክክብ የተፈጸመበት፣ ወደ መጋዘን የገባበትን፣እና የወጣበትን ቀናት በግልጽ የሚያመላክት መሆን ይገባዋል፡፡

## ክፍል አራት

## 4. ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎች

### 4.1. ለኢንተርፕራይዞች የሚደረጉ ድጋፎች

#### 4.1.1. የሥራ ማስኬጃ ብድር

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚዎች በፍጥነት ወደ ምርት እንዲገቡ ማነቆ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን መፍታት አስፈላጊ ነው፡፡ ከእነዚህ ማነቆዎች አንዱ የሥራ ማስኬጃ ፋይናንስ እጥረት ሲሆን ይህንንም ችግር ለመፍታት በየአከባቢው የሚገኝ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ የሥራ ማስኬጃ ብድር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ለታዳጊ መካከለኛ

ኢንተርፕራይዞች ደግሞ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የስራ ማስኬጃ ብድር የሚያመቻቹ ይሆናል፡፡ የብድር አቅርቦቱም ቀደም ሲል የከተማ የብድር አገልግሎት መመሪያ፣ በባንኮች የአሰራር መመሪያ እና ባዘጋጁት የንግድ ሥራ ዕቅድን/ business plan/ መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡

## 4.1.2. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት

በሀገሪቱ የሚገኙ የጥቃቅን አነስተኛ እና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ገበያን መሠረት ያደረጉ እና በጥራት፣ በምርታማነት፣ በጊዜና በዋጋ ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲችሉ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት (የኢንተርፕርነርሺፕ፣ የቴክኒክ የክህሎት ስልጠና፣ የቴክኖሎጂ ልማት አቅርቦት፣ የካይዘን ትግበራ፣ የቴክኖሎጂ እና የጥሬ ዕቃ መረጃ) ይሰጣል።

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን ግልጽ የሆነ መርሀ ግብር በማዘጋጀት ተከታታይ የሆነ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ መሰጠት ያለበት መሆኑ የሚታመን በመሆኑ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ የሚቀርብበት ከተማ ሲመረጥ የተደራጀ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም መኖሩ ወይም በቴክኒክና ሙያ ክላስተር አደረጃጀት የተሟላ ድጋፍ ማድረግ እንደሚቻል መረጋገጥ አለበት፡፡ ስለዚህ የቴክክና ሙያ ተቋሙ የኢንተርፕራይዞቹን የምርት ጥራትና ምርታማነት ለማሳደግ ወሳኝ የሆነ ሚና በመጫወት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞችን ልዩ ትኩረት በመስጠት በክህሎት እና በቴክኖሎጂ የማብቃት ተግባርን የሚያከናውን መሆን አለበት። በዚህም የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ውጤታማ በመሆን ፈጣን የኪራይ አከፋፈል ሥርዓት እንዲኖራቸው ከማስቻሉም በላይ ለኢንዱስትሪ መሠረት የሆኑ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ኢንዱስትሪያሊስቶችን ማፍራት ያስችላል፡፡

## 4.1.3. የገበያ ትስስር

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች በቅድመ ዝግጅት ጊዜ በተጠናው የገበያ ፍላጎት እና የገበያ ምንጮችን መሠረት በማድረግ ከአከባቢ ገበያ እስከ ኤክስፖርት ማድረግ ድረስ ያሉ ዕድሎችን እንዲጠቀሙ ለማድረግ የተቀናጀ

የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በየደረጃው ያሉ የአስፈጻሚ አካላት ቁልፍ ተግባር መሆን አለበት፡፡ ኢንተርፕራይዞች በቀረበላቸው ቴክኖሎጂና ክህሎት ምርቶችን ሲያመርቱ ለአንድ ቀንም ቢሆን የገበያ ችግር ሊያጋጥማቸው ስለማይገባ አስቀድሞ ከፌደራል ጀምሮ እስከ ከተሞች ያለውን የገበያ ዕድሎች በዝርዝር በማጥናት ዕቅድና የማስፈጸሚያ ማኑዋሎች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸውም የተለያዩ የገበያ አቅርቦት ስልቶችን /የንዑስ ተቋራጭነት፣ አውትሶርሲንግ፣ ፍራንቻይዚንግ እና አውት ግሮወር/ በመጠቀም ከታዳጊ መካከለኛ ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ከማስተሳሰር ጀምሮ ለአከባቢው ህብረተሰብ አገልግሎት የሚውሉ ምርቶችን በተለያዩ አለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች በማስተዋወቅ፣ በመንግስታዊ ግዢዎች ሂደትም ከውጪ የሚገቡ የተለያዩ ተኪ ምርቶች በኢንተርፕራይዞች ሲመረቱ የገበያ ትስስር እንዲኖራቸው ምቹ ሁኔታ መፍጠር በየደረጃው ያሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲዎችና ጽ/ቤቶች እና ኢንተርፕራይዞቹ ያከናውናል፡፡

## 4.2. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ የሚደረጉ ድጋፎች

### 4.2.1. የሎጂስቲክ፣ ትራንዚት እና ከቀረጥ ነጻ የካፒታል ዕቃ የማስገባት አገልግሎት

የካፒታል ዕቃ ግዢ የሚፈጸመው ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር የሚያስመጡ አቅራቢዎችን ያካትታል፡፡ የካፒታል ዕቃው በወቅቱ ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ የሚቻለው የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር አቅራቢዎች ወቅቱን ጠብቀው ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አክሲዮን ማህበራቱ የካፒታል ዕቃውን ማቅረብ ሲችሉ ነው፡፡ ይህንን ተግባር በተፋጠነ ሁኔታ ለማከናወን በተለይም ከውጭ የሚገቡ የካፒታል ዕቃዎችን ከመነሻው ቦታ የተለያዩ የመጓጓዣ አማራጮችን /በየብስ፣ በባህርና በአየር/ በመጠቀም የተቀላጠፈና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በወቅቱ መዳረሻ ቦታ እንዲቀርብ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ አቅዶ መስራት አለበት፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የጉምሩክ ቀረጥ አፈጻጸም በሚመለከት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ ማሻሻያ አዋጅ 807/2005 ዓ.ም ለዚህ አገልግሎት የሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ቀረጥ እንደማይከፈልባቸው በመደንገጉ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዕቃው በወቅቱ ለተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች እንዲደርስና ሥራ ላይ እንዲውል ቀልጣፋ

አገልግሎት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የካፒታል ዕቃው ከቀረጥ ነጻ ከገባ በኋላ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን በየወቅቱ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

### 4.2.2. የማማከር አገልግሎት

#### ሀ. የካፒታል ዕቃዎችን ጥራትና ደረጃ የሚያረጋግጥ አማካሪ ድርጅት / Capital Goods Supervisory Service Provider/

አማካሪ ድርጅት መቅጠር ትልቁ ጠቀሜታው የካፒታል ዕቃ ዝርዝር ከማዘጋጀት ጀምሮ መሳሪያው የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠቱን እስከማረጋገጥ ድረስ ያለውን ሥራ ከሙያ እና ከህግ አንጻር ኃላፊነት የሚወስድ ገለልተኛ አካል እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡ ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አክስዮን ማህበራት በፌደራል ደረጃ አማካሪ የሚቀጠር ሲሆን አማካሪ ድርጅቱም ለሁሉም የካፒታል ዕቃ አቅራቢ አክሲዮን ማህበራት በሚገኙበት ቦታ ድጋፍ የሚያደርጉ ባለሙያዎች ይመድባል፡፡ በዋናነት ድርጅቱ የሚያከናውነው ተግባራት የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የማምረቻ መሳሪያዎችን ዝርዝር መግለጫ ያዘጋጃል፡፡ በተዘጋጀው ዘርዝር መግለጫ መሠረት ተወዳዳሪ አቅራቢዎች ያቀረቡትን የቴክኒክ መወዳደሪያ ሰነድ በመገምገም አስተያየት ይሰጣል፡፡ አሸናፊው የካፒታል ዕቃ አቅራቢ ተቋም በተዘጋጀው ዝርዝር መግለጫ (Specification) መሠረት መሳሪያዎቹን ማምረቱን/ ማቅረቡን የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ኩባንያው እንዲረከብ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ በሂደትም የሀገር ውስጥ አቅምን ከመጠቀም አንጻር የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና እና በቴክኖሎጂ ዘርፍ የተሰማሩ ዩኒቨርሲቲዎችን አቅም በማጎልበት መጠቀም የሚቻልበት አማራጭም መታየት አለበት፡፡

#### ለ. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ትግበራ ድጋፍ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት / Implemantation Support Service Consultant/

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት በሀገራችን ተስፋፍቶ የካበተ ልምድ እስከሚገኝ ድረስ አጠቃላይ የአሰራር ሥርዓቱን በተመለከተ ከፍተኛ ልምድ ያለው አማካሪ ድርጅት በመቅጠር ሥራውን መደገፍ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ አሰራር

ጥሩ ልምድ ካላቸው ሀገራት በተመሳሳይ የሥራ ዘርፍ ተሰማርተው ውጤት ያመጡ አማካሪ ድርጅቶችን በመጋበዝ አወዳድሮ  ለተወሰኑ ዓመታት በፌደራል ደረጃ እንዲቀጠር በማድረግ በየክልሉ የሚገኙ የካፒታል ዕቃ አቅራቢ ተቋማትን የፋይናንስ አሰራር ጤናማነትን የማረጋገጥና እና የአቅም ግንባታ ሥራ እንዲያከናውን ይደረጋል፡፡

### 4.2.3. የካፒታል ዕቃ እና የግብዓት የብዛት ግዢ አገልግሎት

በተለያዩ ክልሎች የተቋቋሙ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አከቅራቢ አክሲዮን ማህበራት፣ብዛት ያለው የካፒታል ዕቃዎች ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር አቅራቢ ግዢ በክልል ደረጃ በሚፈጽሙበት ወቅት የፌደራል ኤጀንሲው አስፈላጊውን የአቅራቢዎች ዝርዝር መረጃ እና የማስተባበር ድጋፎች ያደርጋል፡፡ ክልሎች የሚወክሉት የግዢ አካል የኢንተርፕራይዞችን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ብዛት ያለው የጥሬ ዕቃ ግዢ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር እንዲፈጸም ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠር ሥራን ያከናውናል፡፡

### 4.2.4. የፋይናንስ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አክስዮን ማህበራት ወደ ሥራ ሲገቡ የተለያዩ ምንጮችን በመጠቀም የፋይናንስ አቅማቸውን ለማጠናከር የሚያስችላቸውን አሰራር መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ መንግስታዊና ሌሎች የልማት አጋር ድርጅቶች ጋር በትብብር በመስራት እና በቀጣይም ብሔራዊ ባንክ በሚፈቅዳቸው ሌሎች የፋይናንስ አማራጮችን በመጠቀም ለሥራው የሚሆነውን የፋይናንስ አቅርቦት የሚያሟላ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ከንግድ ባንክ ከሚገኝ ብድርና ከመንግስት ትሬዠሪ በሚገኝ ፋይናንስ ድጋፍ የካፒታል ዕቃ አቅራቢ አክስዮን ማህበራቱ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ሊጠቀሙባቸው የሚችሉበት የፋይናንስ ምንጮች ናቸው፡፡ አክስዮን ማህበራቱ ይህንን ፋይናንስ ለማምረቻ መሳሪያ ግዢ እና ለሥራ ማስኬጂያ የሚጠቀሙበት ሲሆን ለሚሰጡትም አገልግሎቶች ተመጣጣኝ የሆነ ትርፍ በየጊዜው በማግኘት ጤናማ የፋይናንስ ዕድገታቸው ቀጣይነት ባለው መልኩ ይረጋገጣል፡፡

## ክፍል አምስት

### 5. የፈጻሚና የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

#### 5.1. ፈጻሚ አካላት

1. **የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ**

- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት የድጋፍ ማዕቀፎችን እንዲቀረጹ ማድረግና በሂደትም እንዲሻሻሉ ያስተባብራል፣
- የካፒታል ዕቃዎች ዝርዝር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይለያል፣ ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት በግብዓትነት እንዲያገለግል ያደርጋል
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት መረጃዎችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ማሰባሰብ፤ ማጠናቀርና ማሰራጨት፣
- ለካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ አቅርቦት እንዲኖር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት በዓይነት ወይም በገንዘብ ሊረዱ የሚችሉ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች እገዛና ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፣
- የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ላይ በማተኮር የሀገር ውስጥና የኤክስፖርት ገበያ ልማት ሥራዎችን ያከናውናል፤

- የዘርፉን የልማት ችግሮች ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያከናውናል፣ አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መቀመርና ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
- በእሴት ሰንሰለት ትግበራ ላይ ኢንተርፕራይዞች የሚታይባቸውን የማምረቻ መሳሪያዎች ክፍተት በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት እንዲሸፈን ያደርጋል፡፡
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይከታተላል ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡
- አማካሪ ድርጅት እንዲቀጠር እና ወደ ሥራ እንዲገባ ያደርጋል፣ የጋራ ግዢ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲከናወን ያስተባብራል
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አክስዮን ማህበራቱን አቅም የመገንባት ሥራ ያከናውናል፡፡

## 2. የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ

- የሥልጠናና የቴክኖሎጂ ልማት ማዕቀፎችን ያዘጋጃል፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መምህራንን አቅም ይገነባል፣
- የበቁ ኢንተርፕራይዞችን የምዘና ማዕከል እንዲሆኑ የሚያስችል ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ለማስፈጸም በክልሎች የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች አቅም መገንባትና ሥራዎቻቸውን ያቀናጃል፤
- ለጥቃቅን፣ አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያገለግሉ የካፒታል ዕቃዎች ዝርዝር መግለጫ /Specification/ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይለያል፣ ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት በግብዓትነት እንዲያገለግል ያደርጋል

- በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በየደረጃው ያሉ አመራሮችና ባለሙያዎች የሃገር ውስጥና የውጭ አገር ተሞክሮዎችን እንዲያገኙ ትምህርታዊ ስልጠናዎችና የልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞችን ማመቻቸትና ውጤታማ የሆነ ድጋፍ እንዲያደርጉ የማብቃት ሥራ ያከናውናል፣
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይከታተላል ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡
- የቴክኖሎጂ አብገር ኢንተርፕራይዞችን አቅም የመገንባት ሥራ ያከናውናል

## 3. የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር

- የወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት ሥራዎች እና የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ሥርዓት ትግበራን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፡፡
- የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶችና ሴቶች ውጤታማ የሥራ ተነሳሽነት ባህል እንዲያዳብሩ የሚስችል አመለካከት በየደረጃው እንዲሰርፅ ያደርጋል፡፡
- የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ በማዘጋጀት የካፒታል ዕቃዎች የሚፈልጉ ወጣትና ሴቶች ስለ መሳሪያ አቅርቦት ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፣
- በልማት ስትራቴጂዎች ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙና ልማታዊ ባለሀብት እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል ፣
- የወጣቶችና ሴቶች የኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ቁጠባን ባህል እንዲያደርጉ እና ከሚያገኙት ገቢ ላይ በስፋት መቆጠብ እንዲችሉ ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ቅስቀሳ እንዲደረግ ያስተባብራል፤
- ውጤታማ የሆኑ ሴቶችና ወጣቶችን በማበረታታት እውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

## 4. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አ.ማ /የከተማ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አ.ማ ቅ/ጽ/ቤት

- ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት የሚውል የሀብት ማፈላለግ፣ የፋይናንስ ምንጮችን የመለየት እና ቁጠባን የማጠናከር ሥራዎችን ያከናውናል፤
- ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት አሰራር የሚያገለግሉ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎችና ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያስተገብራል፤
- የኢንተርፕራይዞችን የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ጥናት ያከናውናል፤ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን ይመለምላል፤
- የካፒታል ዕቃ አምራች/ አስመጪ/ ድርጅትን በመለየት የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ውል ይፈራረማል፣ ማምረቻ መሳሪያዎችን ያስመርታል/ያስመጣል/ በውል ለተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ያስተላልፋል፤
- የካፒታል ዕቃዎቹን ያስተዳድራል፣ ከኢንተርፕራይዞች አቅም በላይ የሆኑ ጥገናዎች እንዲከናወኑ ያደርጋል፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞችን የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል ይደግፋል ብድር ክፍያን ይሰበስባል፤
- ብድሩን በአግባቡ የማይከፍሉ ኢንተርፕራይዞችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 5. የክልል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ /ቢሮ/ የከተማ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት

- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦትን አስመልክቶ በክልሉ የሚዘጋጁ የድጋፍ ማዕቀፎች እንዲቀረጹ ማድረግና በሂደትም እንዲሻሻሉ ያስተባብራል፤
- የካፒታል ዕቃ አምራች/አስመጪ/ ድርጅት በመምረጥ ሂደት፣ በኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ልየታ ላይ ይሳተፋል፣ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም እንዲሳተፉ ያስተባብራል፤
- የማምረቻና መሸጫ ቦታዎች በተለይም ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በከተሞች እንዲገነቡ በጀት ያስይዛል፣የግንባታ እና የማስተላለፍ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት የሚውል ገንዘብ በቁጠባ እንዲሳባሰብ ያደርጋል፣ የብድር አመላለስ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፤

- የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ላይ በማተኮር  የገበያ ልማት ሥራዎችን ያከናውናል፤
- በእሴት ሰንሰለት ትግበራ ላይ ኢንተርፕራይዞች የሚታይባቸውን የማምረቻ መሳሪያዎች ክፍተት በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት እንዲሸፈን ያደርጋል፡፡
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይከታተላል ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦትን በተመለከተ ለተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ ይፈጥራል፣ተጠቃሚዎችን ይመለምላል፣ የአመለካከት ስልጠና ይሰጣል፣
- የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ግንባታን ያከናውናል፣ ያስተላልፋል፣ ያስተዳድራል
- ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር በመቀናጀት የኢንዱስትሪ  ኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲሰጥ ያደርጋል፣
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞችን መረጃዎችን በማጠናቀርና ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፣
- የአከባቢ ገበያ ጥናት በማከናወን ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አጠቃቀምን አስመልክቶ የተሻለ ተሞክሮ ያላቸውን ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮ በመቀመር ለሌሎች የማስፋት ሥራ ያከናውናል

## 6. የክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ/ኮሚሽን/ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት

- በስሩ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ለጥቃቅን፣ አነስተኛና  ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች አገልግሎት የሚውል የካፒታል ዕቃ ልየታ እና ዝርዝር መግለጫ  እንዲዘጋጅ ያስተባብራል፣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።

- ከሥልጠና ማጠናቀቂያ በኃላ ሰልጣኞች የሙያ ብቃት ምዘና እንዲወስዱ ያስተባብራል፣
- የካፒታል ዕቃ አምራች /አስመጪ/ ድርጅት በመምረጥ ሂደት፣ በኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ልየታ ይሳተፉል፣ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት እንዲሳተፉ ያስተባብራል፤
- የበቁ ኢንተርፕራይዞችን የምዘና ማዕከል እንዲሆኑ የሚያስችል እና መሪ መዛኝ የማፍራት ሥራዎች ያከናውናል፤
- በክልሉ ለሚሰራው የሰው ኃይል ልማትና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ማንዋል ዝግጅት ያስተባብራል፣
- ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት መምህራን የክህሎት ክፍተታቸውን በማጥናት ተጨማሪ ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚ ለሆኑ ልዩ ፍላጎት ላላቸውና ሞዴል ለሆኑ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልዩ የሥልጠናና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
- ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚዎች የቴክኒክ እገዛ በማድረግ በተመጣጣኝ ዋጋ የመለዋወጫ ዕቃዎችን በመሥራት የመሳሪያ ጥገና ሥራዎችን ያከናውናል፣
- በማምረቻ መሳሪያ ጥገና አገልግሎት ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በሥራቸው የበቁ ይሆኑ ዘንድ ሥልጠናና ድጋፍ ይሰጣል፣
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከማምረቻ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች ጋር በተያያዘ ያሉባቸውን ችግሮችና ክፍተቶች በተመለከተ ዝርዝር ጥናት ያደርጋል፣
- ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ስለ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት አጠቃቀም፣ አያያዝና ጥገና ሥልጠናና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
- የካፒታል ዕቃ ከአቅራቢው ወደ አክስዮን ማህበሩ እና ከአክስዮን ማህበሩ ወደ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ርክክብ ሲደረግ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

7. **የክልል አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት /የከተማ አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት**

- ለብድር አሰጣጥ እና ለቁጠባ አሰባሰብ የሚጠቅሙ ዝርዝር የአሰራር መመሪያዎችና ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤
- አነስተኛ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋም ለደንበኛ ተደራሽነቱን ይበልጥ በማስፋት፤ የደንበኞችን የገንዘብ ደህንነት አስተማማኝ በማድረግ፤ ቀልጣፋና ምቹ አሰራርን በመዘርጋት፣ የተለያዩ ጠቀሜታ ያላቸውን የቁጠባ አይነቶችን በመቅረፅ እና አደረጃጀታቸውን የበለጠ ምቹ በማድረግ በቁጠባ ላይ በስፋት ይሰራል፤
- የቁጠባ ዕቅዱን አፈፃፀም ከሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላት ጋር በመሆን በየጊዜው በመገምገም አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በማድረግ የገንዘብ አቅርቦትን ካለው የብድር ፍላጎት ጋር የማጣጣም ሥራዎች ያከናውናል፤
- የኢንተርፕራይዝ ቤተሰቦች ለልጆቻቸው የስራ ባህል እንዲያስተምሩና የቅድመ ብድር ቁጠባ እገዛ በማድረግ፤ ዋስትና በመግባት፤የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ እንዲያውሉ በመከታታል፤በብድር አመላለስና ቁጠባ እንዲሁም በአጠቃላይ በኢንተርፕራይዞቹ ሁለንተናዊ ድጋፍ ላይ የራሳቸውን ሚና እንዲጫወቱ ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ይሰራል፡፡
- ብድር ለመውሰድ ለተመለመሉ ደንበኞች ስለ ብድር እና ቁጠባ ጠቀሜታ፣ የብድር አሰጣጥና አመላለስ ሂደቱ አስመልክቶ፣ የደንበኛው መብቶችና ግዴታዎች ላይ ስልጠና ይሰጣል፤
- ደንበኛው ስለሚያዘጋጀው የንግድ የሥራ ዕቅድ እና ስለሚፈልገው የብድር መጠን በአግባቡ ግንዘቤ እንዲያገኝ ያደርጋል፣
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የሥራ ማስኬጃ ብድር ያቀርባል፣
- የኢንተርፕራይዞቹን የብድር አጠቃቀም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የተሰጠውን ብድር በወቅቱ ያስመልሳል፣ በማይመልሱት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

8. **የክልል የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ /የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት**

- የካፒታል ዕቃ ፈላጊ ወጣቶች እና ሴቶች በአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያ እንዲመዘገቡ በየአደረጃጀታቸው ቅስቀሳ በማድረግ ግንዛቤ ያስጨብጣል፣
- የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶችና ሴቶች ውጤታማ የሥራ ተነሳሽነት ባህል እንዲያዳብሩ የሚስችል አመለካከት እንዲሰርፅ ያደረጋል፡፡
- የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ በማዘጋጀት የካፒታል ዕቃዎች የሚፈልጉ ወጣትና ሴቶች ስለ መሳሪያ አቅርቦት ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፣
- በልማት ስትራቴጂዎች ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙና ልማታዊ ባለሀብት እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል ፣
- ወጣቶችና ሴቶች ቁጠባን ባህል እንዲያደርጉ በተፈጠሩ አደረጃጀቶች ግንዛቤ ያስጨብጣል፣
- የወጣቶችና ሴቶች የኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ከሚያገኙት ገቢ ላይ በስፋት መቆጠብ እንዲችሉ ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ቅስቀሳ መደረጋቸውን ይከታተላል፣

## 9. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ

- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦትን በተመለከተ ለተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ግንዘቤ ይፈጥራል፣ተጠቃሚዎችን ይመለምላል፣ የአመለካከት ስልጠና ይሰጣል፣
- አዲስ ወደሥራ ለሚገቡ ሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ያከናውናል፣ ህጋዊ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤
- የካፒታል ዕቃዎችን እና ውሎችን ይመዘግባል፣ ያድሳል ይሰርዛል፡፡
- ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽ አገልግሎት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በተሟላ ደረጃ ያደራጃል፣ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፡፡

- የአከባቢ ገበያ ጥናት በማከናወን ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፤
- የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ያስተላልፋል ያስተዳድራል፤
- ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት የሚውል ቁጠባ እንዲሰባሰብ ያደርጋል፣ የብድሩ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞችን በመደገፍ ብድሩን ኢንዲመልሱ ክትትል ያደርጋል፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞችን መረጃዎችን በማጠናቀር ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፣

## 5.2. አስፈጻሚ አካላት

### 1. የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

- የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት እና አሰራሮች በማጥናት ለመንግሥት አቅርቦ ማስወሰን፣ አፈጻጸሙን መከታተል፤
- ከተሞች የዘርፉን ልማት እንዲደግፉና በባለቤትነት እንዲፈጽሙ ያስተባብራል፤
- የዘርፉን የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያስተባብራል፤
- በዘርፉ ልማት ሚና ያላቸውን አካላት በማቀናጀት በየሦስት ወሩ ሁሉም ፈጻሚ አካላት ባሉበት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በማካሄድ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤

### 2) የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

- የካፒታል ዕቃ መረጣ፣ ዝርዝር መግለጫ ማዘጋጀት እና የአጠቃቀም ስልጠናዎች ላይ ይሳተፋሉ፣
- የጥቃቅን፣ አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ከመካካለኛና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር የገበያ ትስስር እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፤
- ከአነስተኛ ወደ ታዳጊ መካከለኛ ለሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞችልዩ ትኩረት በመስጠት የምርት ልማትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ኢንተርፕራይዞችን የማብቃት ሥራ ያከናውናሉ፤

3) **የንግድ ሚኒስቴር**

- ለጥቃቅን፣ ለአነስተኛ፣ ለታዳጊ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርቡ የካፒታል ዕቃዎችን ይመዘግባል፤
- ስለተመዘገቡት የካፒታል ዕቃዎችና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶች የመረጃ ስርዓት ይገነባል፣ የተሟላ መረጃ ይይዛል፤ እንዲያዝም ያደርጋል፤
- ለተመዘገቡ የካፒታል ዕቃዎች የተሰጡ መለያ ቁጥሮች በዕቃዎቹ ላይ መለጠፋቸውን ይቆጣጠራል፤
- የካፒታል ዕቃዎቹ ለምርመራ የሚቀርቡበትን ቦታና ጊዜ ወይም ባሉበት ቦታ እንዲመረመሩ ይወስናል፤ የምርመራ ሂደትን ያስተባብራል፤
- የካፒታል ዕቃዎችና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶች ምዝገባ እንዲከናወን ለአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ወይም ሌላ አግባብ ላለው አካል እንዳስፈላጊነቱ ውክልና ይሰጣል፤
- የካፒታል ዕቃ ምዝገባ የሚታገድበት ወይም የሚሰረዝበት ሁኔታ ሲያጋጥም በማስረጃ በማጣራትና በማረጋገጥ ምዝገባውን ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤
- ከካፒታል ዕቃዎች ምዝገባ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ህዝብ ሊያውቀው ይገባል ብሎ ያመነበትን መረጃ ይፋ ያደርጋል፡፡

4) **የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ**

- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ሕጎችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት እንዲተገበሩ ያደርጋል አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
- ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የስራ ፈቃድ ይሰጣል፣ የተቋማቱን ሥራዎች ያስተባበራል ያቀናጃል፤
- የሌሎች ሀገራትን ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር፣ ተሞክሮውን በማሰራጨት አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን አቅም ይገነባል፡፡

5) **የክልል ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮዎች/የክልል የቤቶች ልማትና ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ፣ የከተማ አስተዳደሮች፣የከተማ ንግድ ልማት ጽ/ቤት፣ማዘጋጃ ቤቶች/**

- በክልሉ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት እና ተያያዥነት ያላቸው አሰራሮችን የሚሻሻሉ ህጎችን ማጥናትና ለክልሉ መንግሥት ማቅረብ፣ ሲፈቀድም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
- ከተሞች የዘርፉን ልማት እንዲደግፉና በባለቤትነት እንዲፈጽሙ ያስተባብራል፤
- የክልሉን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያስተባብራል፤
- በዘርፉ ልማት ሚና ያላቸውን አካላት በማቀናጀት በየወሩ ሁሉም ፈጻሚ አካላት ባሉበት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት አፈፃፀም ግምገማ በማካሄድ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤

- የካፒታል ዕቃዎችና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶች ምዝገባ ለማከናወን የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ወይም ሌላ አግባብ ላለው አካል ውክልና መሰጠቱን ያረጋግጣል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- የማምረቻና የመሸጫ ክላስተር ማዕከላት ግንባታ ፣ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያዎችን ለአፈጻጸም በሚያመች መልኩ እንዲሻሻል ያደርጋል፣
- የማምረቻ፣ የመሸጫና ገበያ ክላስተር ማእከላት ግንባታን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ አፈጻጸሙን ይገመግማል፣
- የማምረቻ፣ የመሸጫና ገበያ ክላስተር ማእከላት ግንባታና መሰረተ ልማት አገልግሎት የሚውል በጀት ከክልል መንግስት ለከተማ አስተዳደር እንዲመደብ ያደረጋል፡፡
- ለማምረቻ፣መሸጫና ገበያ ማእከላት የሚሆኑ ቦታዎችን የቦታ ዝግጅት መረጣ በመስፈርቱና በከተሞች እደገትና ማስተር ፕላን መሰረት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ ለሆኑ ኢንተርፕራይዞች ለማምረቻ አገልግሎት እንዲውሉ ለተመረጡ ቦታዎች አስፈላጊውን መሰረተ ልማት/መብራት ፣ መንገድ፣ ውሃ፣ ስልክ/ እንዲሟላ ያደርጋል፣
- በሀገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ስታንዳርድና ዲዛይን መሰረት ለከተማው የተመረጠውን ቦታ ታሳቢ ያደረገ ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን ያዘጋጃል፣
- የማምረቻና መሸጫ ክላስተር ማእከላት ቦታ ካርታና የግንባታ ፈቃድ አዘጋጅቶ ለከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ለማስረከብ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣
- የማምረቻና መሸጫ ገበያ ክላስተር ማዕከላት ግንባታ ወጭ ቆጣቢ አሰራረሮችን በመከተል ኢንዱስትሪ መንደሮችን፣ ህንጻዎችንና ሼዶችን እንዲገነቡ ያደርጋል፣
- ለማምረቻና መሸጫ የገበያ ማእከላት ግንባታ ክልሉ ከሚመድበው በተጨማሪ በጀት ይመድባል፡፡

## 5.3. ባለድርሻ አካላት

### 1. የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን /የክልል/የአዲስ አበባ/ ገቢዎች ቢሮ

- የካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 እና ተሻሻሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 807/2005 ዓ.ም መሠረት የካፒታል ዕቃ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ያደርጋል፤
- ከቀረጥ ነጻ የገቡ የካፒታል ዕቃዎች ለታለመው አላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
- የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ በመሆን ወደ ሥራ የሚገቡ እና ሥራዎቻቸውን የሚያስፋፉ አንቀሳቃሾች ምርት አምርተው ወደ ገበያ በሚገቡበት ወቅት ግብር መክፈል እንዳለባቸው የግንዛቤ ማጨበጫ ስልጠና ይሰጣል፡፡

2. የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን

- የተመረጡ ኢንተርፕራይዞች ምን ዓይነት የማምረቻ መሳሪያ እንደሚፈልጉ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ፍላጎታቸውን ይለያል፣
- በፍላጎት መሠረት ከተመረጡት መሳሪያዎች መካከል ከስትራቴጂው አንጻር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የሥራ ዘርፎች በመለየትተስማሚነታቸውን ያረጋግጣል፤
- የተመረጡ መሳሪያዎችን በማምረት ወይም ከውጭ ሀገር በማስገባት ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- ለሚያቀርባቸው የካፒታል ዕቃዎች በውሉ መሠረት የጥገናና ዕድሳት ሥራዎች ያደርጋል፤
- የማምረቻ መሳሪያዎቹ አጠቃቀም ላይ ስልጠና ይሰጣል፤

3. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

- በየክልሉ ለተቋቋሙ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አክስዮን ማህበራት የረጅም ጊዜ ብድር አገልግሎት ይሰጣል፤
- የተሰጠውን ብድር በሚመለከት ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አክስዮን ማህበር የምክር አገልግሎትና አቅም ግንባታ ሥራ ያከናውናል ፡፡
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን አቅም ይገነባል፡፡
- ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሥራ ማስኬጃ ብድር ያመቻቻል፡፡

## 4. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

- ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጠቀሜታ ያላቸውን ተፈላጊና አዋጭ ቴክኖሎጂዎችን በጥናትና በምርምር በመፍጠር ያስተዋውቃል፣
- ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች በአካባቢና በቀላል ጥሬ ዕቃ እንዲመረቱ የሚያስችል ጥናትና ምርምር በማድረግ ውጤቱን ለተለያዩ ተቋማት ያስተዋውቃል፣
- በተመረቱ ቴክኖሎጂዎች እና በቀረቡ የካፒታል ዕቃዎች አጠቃቀምና አሰራር ዙሪያ ለጥቃቅንና አነሰተኛ ተቋማት ስልጠና፣ የምክር አገልግሎት እና አስፈላጊ መረጃዎች ይሰጣል።

## 5. የኢትዮጵያ የባህር ትራንዚትና ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት

- በኢትዮጵያ ንግድ መርከብ የሚጫኑ የካፒታል ዕቃዎች በተቀላጠፈ መንገድ ወደ ሀገር እንዲገቡ ያደርጋል፤
- ወደብ የደረሱ የካፒታል ዕቃዎችን ከአቅራቢው ጋር በሚደረገው ስምምነት መሠረት በአፋጣኝ ወደ መዳረሻው የማጓጓዝ አገልግሎት ይሰጣል፤

## 6) የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚዎች ኃላፊነት

- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ የሚሆነው ኢንተርፕራይዝ ሙሉ ፍላጎት ያሳየ መሆን ይኖርበታል፣
- ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙም ሆነ ለሌላ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ላለው አካል ትክክለኛ መረጃ ይሰጣል፣

- በካፒታል ዕቃ ፋይናነስ የቀረበለትን ማምረቻ መሳሪያዎች በአግባቡ በመያዝ የመጠቀም፣ የመንከባከብ እና መጠገን ኃላፊነት አለበት፤
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ብድርን በወቅቱ የመክፈል ግዴታውን ይወጣል፣
- ኢንተርፕራይዙ ከአቅራቢው ተቋም የሚረከበውን የካፒታል ዕቃ በወቅቱ የማስመዝገብ፣ የማስመርመርና የማስፈተሽ ኃላፊነት ይወጣል፣
- ከማምረቻ መሳሪያዎች አጠቃቀም ጋር ተያይዞ ያጋጠማቸውን ችግሮች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፣በአቅማቸው የሚሰራውን የጥገናም ሆነ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤
- የካፒታል ዕቃ ተከራይ የተከራየውን መሳሪያ በሰራተኛ ጉዳት እንዳያደርስ መከላለከል አለበት፣ ለሚያደርሰው አደጋ ወይም ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
- የካፒታል ዕቃ ተከራይ የተከራየውን መሳሪያ ሙሉ ዕቃና መለዋወጫ ከስርቆት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡
- የካፒታል ዕቃ ተከራይ ውጤታማ ተጠቃሚ መሆን የሚችለው የተከራየውን መሳሪያ ክህሎት ባለው ባለሙያ እንዲንቀሳቀስ ሲያደርግ መሆኑን ተረድቶ መስራት አለበት፡፡

## 6. የድጋፍና ክትትል ሥራዎች

ለተጠቃሚዎች የተላለፈውን የካፒታል ዕቃ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን /መሳሪያው መጥቶ መተከሉን/ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን በቦታው ላይ ሆኖ መስራቱን ማወቅ ንብረቱ ከጥፋትና ከጉዳት ለመከላከልና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ገቢ እያስገኘ መሆኑን ተጠቃሚው እና ህብረተሰቡ ከአገልግሎቱ የተጠቀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ ስለሆነም የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አክስዮን ማህበሩ፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት፣

የአንስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋም እና የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ጋር በመሆን የሚከተሉት ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

- መሳሪያዎቹ በተቀመጡበትና በተተከሉበት ቦታ ላይ ሆነው በመስራት ላይ መሆናቸውንና ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ቢያንስ በየወሩ በፈጻሚ አካላት ይታያሉ፤
- መሳሪያዎቹ በሙሉ አቅም፣ በጥንቃቄ እና ከአደጋ ነጻ በሆነ መንገድ መያዛቸውንና ሥራ ላይ መሆናቸውን ክትትል ይደረጋል፤
- በመሳሪያዎቹ አጠቃቀም ላይ የክህሎት ክፍተት ያለመኖሩን፣ ገበያው የሚፈልገውን ምርት በጥራት በማምረት ላይ መሆናቸውን ከተጠቃሚዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በመገምገም የመፍትሔ አቅጣጫ ይሰጣል፤
- መሳሪያዎቹ በኪራይ ወይም በትውስት ለሦስተኛ ወገን አለመተላለፋቸው ክትትል ይደረጋል፤
- የአቅራቢው ተቋም በመሳሪያዎቹ ላይ ያደረገውን ዓርማና መለያ ቁጥር በቦታው መኖሩን፣ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዙ ውጤታማ ሆኖ ክፍያውን ያለማቋረጥ እየከፈለ መሆኑን፣ መሳሪያው ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ አለመደረጉን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓቱን ጠቀሜታ ለማስፋፋትና ለማጠናከር አስፈላጊው ጥረት የሚደረግ ይሆናል፡፡

7. የመረጃ አያያዝና ሪፖርት ሥርዓት

በየደረጃው የሚገኙ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አካላት የተለያዩ የመረጃ አያያዝ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚከተሉትን መረጃዎች በመያዝ በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሀ. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞችን እና የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ዝርዝር መረጃ፣

ለ. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞችን የካፒታል ዕቃ ፍላጎት መሠረት በማድረግ የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ የመሳሪያ ዓይነት ዝርዝር ካታሎግ መረጃ ፤

ሐ. የካፒታል ዕቃ አቅራቢ ተቋማት ዝርዝር/Short list/ መረጃ፣

መ. የተገዙና በግዢ ሂደት ላይ ያሉ እና ከተለያዩ መንግስታዊ መንግስታዊ ካለሆኑ አካላት በድጋፍ የተሰጡ የካፒታል ዕቃዎች ዝርዝር መረጃ

ሠ. የተላለፉ የካፒታል ዕቃዎች ዓይነት ዝርዝርና መረጃ፣

ረ. የተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ካፒታል ዕቃ ያለበት ሁኔታ እና የኪራይ ክፍያ አሰባሰብ መረጃ

ሰ. የተጠቃሚዎች ዝርዝር መረጃ (ስም፣ አድራሻ፣ የሥራ አይነት፣ የዕድገት ደረጃ፣ የወሰደው የካፒታል ዕቃ አይነትና መጠን፣ የኪራይ ክፍያ መጠንና ጊዜ፣ የወለድ መጠን፣ ወዘተ..)

ሸ. በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ለባንክ የሚከፍለው የብድር ክፍያ መጠን መረጃ

የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰበት በመሆኑ በየደረጃው ያሉ ቅርንጫፍ መስሪያቤቶች በዘመናዊ የሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማት በመጠቀም ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በየወሩ ለክልሉ የካፒታል ዕቃ አቅራቢ አክስዮን ማህበር እና ለከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

የክልሉ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አ.ማ በየወሩ አክስዮን ማህበሩን ለሚመራው ቦርድ እና ለክልሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ምክር ቤት

ሪፖርት የሚያቀርብ ሲሆን በየሦስት ወሩ ደግሞ ለብሔራዊ ባንክና ለፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ምክር ቤት ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ሪፖርት የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

## 8. ማጠቃለያ

የሀገራችን ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማስቀጠልና የግብርናውን ኢኮኖሚ ደረጃ በደረጃ ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ትኩረት አድርጎ የርብርብ ማዕከል ማድረግ ወሳኝ ነው ፡፡ ስለሆነም በዘርፉ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞችን እንዳያድጉ አንቀው የያዛቸውን ማነቆች በዝርዝር በመለየትና በተቀናጀ ድጋፍ በጋራ በመፍታት ኢንተርፕራይዞችን በገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማስቻል የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት ማረጋገጥ ጊዜ የማይሰጠውና አንገብጋቢ የልማት ጥያቄ ነው፡፡

ዘርፉ ባለፉት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ትግበራ ዓመታት በከተሞች ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ሥራ አጥነትና ድህነት ከመቀነሱም ባሻገር ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ የጎላ ድርሻ እንደነበረው ይታወቃል፡፡ በትግበራ ወቅት በዘርፉ የታዩ ማነቆዎች ሰፊ የአመለካከት ችግር ፤የቴክኖሎጂ፣ የክህሎትና የገበያ ችግሮች በመሆቸው እነዚህ ማነቆዎች ከመፍታት አንጻር በአንድ በኩል በዘርፉ ልማት ላይ በእንቅፋትነት የተለዩትን የኪራይ ሰብሳቢነትና የጠባቂነት አመለካከቶችን ለማስወገድ በየደረጃው ባሉ አስፈጻሚ አካላት ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ነው፡፡ በሌላ በኩል በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ልማት ማነቆ የሆነውን ቴክኖሎጂ አቅርቦት ለመፍታትና ለኢንዱስትሪ ልማት መሠረት በመጣል ከታዳጊ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በንዑስ ተቋራጭነትና በአውት ሶርሲንግ ማስተሳሰር ይገባል፡፡ በከተሞች የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲቻል በየክልሉ የካፒታል ዕቃዎች ፋይናንስ ሥርዓት በመዘርጋት እና አስፈላጊ የሆነውን የመነሻ ካፒታል በማዘጋጀት የኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ ባሻገር ልማታዊ ባለሀብት ለመፍጠር አይነተኛ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓቱን በላቀ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዳ የተዘጋጀው የአሰራር ማኑዋል የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት

ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አሰራር ሥርዓት፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አሰራር ሥርዓት ድጋፎች፣ የፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም የድጋፍና ክትትል ሥራዎችን በዝርዝር የያዘ ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡፡

| ተ.ቁ. | የሀብት ዓይነት | B²T | yxNÇ êU | «Q§§ êU |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| | | | | |

m.<u>በኪራይ  ለመውሰድ የፈለጉት የካፒታል ዕቃ መረጃ</u>

| t.qÜ | የካፒታል ዕቃው ዓይነት | የmúሪያW «q»¬ | yxNÇ ግምታዊ êU | «Q§§ ግምታዊ êU | ዝርዝር መግለጫው |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

¿.ywÀÂ gbþ mr©

*1. <u>ለሥራ ማስኬጃ የሚያስፈልጉ ወጪዎች</u>*

| | ZRZR *wÀãC* | m«N | yxNÇ êU | |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

## 2. l¤lÖC wÀãC

| | ZRZR | m«N | yxNÇ êU | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

## 3. gbþ

### 13.1 wC¼êE yMRT ሺ.ዖዌ GMT

| yMRT ዓYnT | መ«N | yxNÇ êU | «Q§§ êU |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

### r. y>Au hùn¤¬ mr©

yxþNtRP‰Yzù MRtÜN bMN ›YnT mNgD Y¹ÈL?

bcRÒé--------------------

bJM§ xkÍÍ×C-----------------------

ኢንተርፕራይዙ bCRÒé y¸¹_ kçn ym>Å ï¬ xlW? ----------------------

**s. y_bÝ êSTÂ mr©**

y_bÝ êSTÂ lNBrtÜ y¸s«W ¥nW ? ----------------------------------------------

yxmLµC SM ___________________________

ðR¥ ________________________

qN__________________________

## II. የካፒታል ዕቃ ኪራይ ውል

----------- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አ.ማ

### የካፒታል እቃ ኪራይ ውል

ይህ ውል ------------------------------------ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አ.ማ ከዚህ በኋላ አከራይ በሚል የሚጠራው አድራሻ ------------- ክ/ከተማ -------- ቀበሌ ----------- የቤት ቁጥር ---------------- እና ከዚህ በኋላ ተከራይ ተብሎ በሚጠራው አቶ/ወ/ሮ/ት ------------------------------------ /ወረዳ/ክ/ከተማ ---------------- ቀበሌ ------------------ የቤት ቁጥር ----------------------ስ.ቁ ዛሬ -------------------- ቀን ------------ ዓ/ም መካከል የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነት ውል ተደርጓል፡፡

### አንቀጽ አንድ

### የስምምነቱ አላማ

አከራይ ዋጋው ብር ------------------ / -----------------------------------------
የሚያወጣ የ ------------------------------------------------- ካፒታል እቃ ከ --------------
---------------- አቅራቢ/አምራች የተገዛ ለተከራይ በዱቤ ግዥ/በፋይናንሻል ኪራይ በኪራይ ለመስጠት እና ተከራይም የካፒታል እቃውን ዋጋ ብር -----------------------
------/ ---------------------------------/ --------------------% ቅድሚያ ክፍያ ለመክፈል የተደረገ ስምምነት ነው፡፡

## <u>አንቀጽ ሁለት</u>

## <u>የክፍያ ዘመን</u>

የካፒታል እቃ ኪራይ ተከራዩ በብር -----------------------/------------------------------
----- ተገዝቶ የተሰጠውን የካፒታል እቃ ዋጋ ላይ በቀጥታ ስሌት የሚታሰብ -------
----------------% ወለድ እና በአጠቃላይ የካፒታል እቃ ዋጋ መጠን ላይ የሚታሰብ -------------------------% የአገልግሎት ክፍያ ለመክፈል የተስማማ ሲሆን በተጨማሪም ከ -------------------------- ቀን ------------------- ዓ/ም ጀምሮ በየወሩ/በየሩብ ዓመቱ ብር ------------------ /----------------------------------------------/
የዋና ዕዳ፣ ብር ----------------/ -----------------------------የወለድ፣ ብር -------------------
-------/ ----------------------------------------------/ የአገልግሎት ክፍያ ብር --------------
----------- በአጠቃላይ ብር -------------------/ ----------------------------------------/
እየከፈለ እስከ ------------------------------------------- ዓ/ም ወይም ከዚያ በፊት ክፍሎ ለማጠናቀቅ ግዴታ ገብቷል፡፡

## <u>አንቀጽ ሶስት</u>

## የተከራይ ግዴታ

ተከራይ የወሰዱትን የ -------------------------------- የካፒታል እቃ

ሀ. በዚህ ውል አንቀጽ 2 በተገለፀው መሰረት ወርሃዊውን/በየሩብ ዓመቱ ክፍያውን በወቅቱ መክፈል አለበት፡፡

ለ. የካፒታል ዕቃ ኪራይ ክፍያ ያቋረጠ ተከራይ በተሰጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያውን የማይከፍል ከሆነ የካፒታል ዕቃውን ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ለአከራይ የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

ሐ. በዚህ ውል አንቀጽ 2 በተገለፀው መሰረት ወርሃዊውን/የሩብ ዓመቱን ክፍያው በወቅቱ ያልከፈለ ተከራይ የክፍያውን 5% በክፍያው ላይ ጨምሮ ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

ሠ. ተከራዩ የተሰጠው የካፒታል እቃ በምንም መንገድ ለሌላ ሶስተኛ ወገኖች የማይሰጥ መሆኑን ተከራዩ ተስማምቷል፡፡

ረ. የካፒታል እቃው ላይ የተቀመጠው መለያ ምልክት እና ቁጥሮች በጥንቃቄ ከብልሽት በፀዳ መልኩ ይጠበቃል፡፡

ሰ. የካፒታል እቃው በአከራይ አማካኝነት ለተከራይ ርክክብ ተፈጽሞ ከወሰደው በኋላ የካፒታል እቃው አመራረት ግድፈት ካለሆነ በስተቀር የካፒታል እቃው ጥራት ቅሬታ ማቅረብ እንደማይቻል ተስማምቷል፡፡

ሸ. በኪራይ የተሰጠውን የካፒታል እቃ መጠቀም የሚችሉትና የሚያንቀሳቅሱት በአጠቃቀም መመሪያው መሰረት ሙያ ያላቸው ሰራተኞች ሲሆኑ ለተሰማሩበት ስራ ብቻ ለመዋል የተስማማ መሆኑን ግዴታ ገብቷል፡፡

ቀ. ተከራይ በካፒታል ዕቃው ላይ በአከራዩ የተለጠፈውን አርማ የያዘ መለያ ቁጥር /ታግ/ ማንሳት ወይም መለወጥ አይችልም፡፡

## አንቀጽ አራት

## ልዩ ልዩ ግዴታዎች

4.1. በካፒታል ዕቃ መጥፋት ወይም መበላሸት ምክንያት የኪራይ ውሉ ሊቋረጥ አይችልም፡፡

4.2. የኢንሹራንስ አረቦኑ በተከራይ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

4.3. በካፒታል እቃው ላይ ከባድ ብልሽት ወይም የመጥፋት አደጋ ካጋጠመ ተከራይ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለአከራይ ወዲያውኑ የማሣወቅ ግዴታ እንዳለበት፡፡

4.4. በአደጋ ወይም በስርቆት ምክንያት ኢንሹራንስ የሚከፈለው ገንዘብ ለአከራዩ ሆኖ የኢንሹራንስ ክፍያም የካፒታል እቃውን ለመተካት እንዲውል ይደረጋል፡፡ ሆኖም ክፍያው ሙሉ በሙሉ ዕቃውን ለመተካት የማይችል ከሆነ ቀሪ ክፍያውን ተከራይ ይሸፍናል፡፡

4.5. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ኢ.ማ ባስፈለገው ጊዜ የተከራዩን ሂሳብ የማየትና  እንቅስቃሴውን መመርመር ይችላል፡፡

4.6. የኪራይ ዘመኑ ተጠናቆ እዳው በሙሉ ተከፍሎ ሲዘጋ የካፒታል እቃ ስም ዝውውር በሚደረግበት ጊዜ ለባለቤትነት ሁኔታ የሚያበቃውን ክፍያ በሙሉ ተከራዩ እንደሚሸፍን ግዴታ ገብቷል፡፡

## <u>አንቀጽ አምስት</u>

## <u>የአከራይ ግዴታ</u>

5.1. አከራዩ የካፒታል ዕቃውን ከአቅራቢ በመረከብ የማምረቻ ቦታ ድረስ በመጓጓዝ የተከላና ኮሚሺኒንግ ሥራዎችን በማጠናቀቅ ለተከራይ ያስረክባል፡፡

5.2. አከራይ ውሉ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ወለድ የሚከፈልበት የ------------------ወር የእፎይታ ጊዜ ለተከራዩ ይሰጣል፡፡

5.3. ለኪራይ የሚውለውን የካፒታል እቃ ክፍያ በስሙ ይፈጽማል፡፡

5.4. ተከራይ ክፍያውን ቢያቋርጥ አከራዩ የ30 ቀናት ማስጠንቀቂያ የመስጠት እና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ክፍያውን የማይቀጥል ከሆነ የካፒታል ዕቃውን መልሶ ይረከባል፡፡

5.5. አከራይ የካፒታል እቃውን በካፒታል እቃ እና ውል ስምምነት ምዝገባ ደንብ መሰረት የባለቤትነት ሰነድ በ ------------------ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ወይም እንደአግባብነቱ ህጋዊ ስልጣን በተሰጠው አካል የካፒታል ዕቃው እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ያስመዘግባል፡፡

## አንቀጽ ስድስት

## የካፒታል እቃ ባለቤትነት ስም ዝውውር

ተከራዩ የሚፈለግበትን ክፍያ አጠናቆ ከከፈለ በኋላ የካፒታል እቃው ባለቤትነት ስም ለማዘዋወር የሚያስፈልጉ ወጪዎችን በመሸፈን ዝውውሩኑን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ ሰባት

## የውሉ አፈፃፀም

በዚህ ውል የተገለፀውን መብትና ግዴታዎች ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች የተስማማንባቸው ቢሆንም ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መፈፀም የማያስችል ሆኖ ከተገኘ እንደአግባብነቱ በፍትሐብሄር ህግ መሰረት ለመፈፀም ግዴታ ገብተን ተፈራርመናል፡፡ ይህ ውል ዛሬ ----------------- ቀን ----------- ዓ/ም ተፈረመ

**ስለ አከራይ ስለተከራይ**

ስም ----------------------------------- ስም ----------------------
---------

ፊርማ -------------------------------- ፊርማ --------------------
---------

ቀን ------------------------------------ ቀን ----------------------
----------

## ምስክሮች

| ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| 1. -------------------------------- | ----------------------------- | ----------- -------- |
| 2. -------------------------------- | ----------------------------- | ----------- -------- |
| 3. -------------------------------- | ----------------------------- | ----------- -------- |

### III. የካፒታል ዕቃ መረካከቢያ ቅጽ

-------------------------- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አ.ማ

የ ----------------------- ካፒታል እቃ መረካከቢያ ቅጽ

1. የተረካቢ ስም፡- ------------------------------------------------------------

አድራሻ ፡- --------------------/ወረዳ/ክ/ከተማ--------------- ቀበሌ ----------

የቤ.ቁ --------

ስልክ የመኖሪያ ቤት ----------------------------------- የቢሮ-------------------

2. የአስረካቢ ስም -------------------------------------------------------------

አድራሻ፡- --------------------  ክ/ከተማ --------- ቀበሌ ------------ የቤ.ቁ --------------

ስልክ  ---------------------------  ------------------------  ----------------------

የካፒታል እቃውና ተጓዳኝ ዕቃዎች (accessories) ዝርዝር

| ተ.ቁ | ዝርዝር | | የአንዱ ዋጋ | | ጠቅላላ ዋጋ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብር | | ብር | ሣ | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | ድምር | | | | | | |

አቶ/ወ/ሮ ---------------------------------- የ ------------------- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ኢ.ማ ያከራየውን --------------------------------- የካፒታል እቃ ከላይ በተመለከተው ሰንጠረዥ ከተ.ቁ ------------------ እስከ ------------- የተዘረዘሩትን የካፒታል እቃ እና ተጓዳኝ ዕቃዎች (accessories) አቶ/ወሮ ------------------------------------------ የ ----------------------------- ተወካይ የካፒታል እቃ እና ተጓዳኝ ቁሳቁሶችን አንድ በአንድ ቆጥሬና አረጋግጨ የተረከብኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**አስረካቢ**

ስም ----------------------------------------

ፊርማ -------------------------------------

ቀን -----------------------------------------

**ተረካቢ**

ስም ------------------------------

ፊርማ ---------------------------

ቀን ------------------------------

**ምስክሮች**

1. ስም ----------------------- ፊርማ ------------------------ ቀን ---------------
2. ስም------------------------- ፊርማ ------------------------ቀን ----------------
3. ስም -------------------------- ፊርማ ----------------------ቀን ---------------

## IV. ግዴታውን ለማይወጣ ተከራይ የሚሰጥ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ

ቀን ------------------------

ለ -------------------------------

ባለቤት -----------------------

**<u>በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1772 መሰረት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ</u>**

እርስዎ ከ --------------- የካፒታል እቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አ.ማ ጋር ---------------- ቀን ----------- ዓ/ም በተደረገው ውል መሰረት ----------------ብር የሚያወጣ---------------------------------- የካፒታል ዕቃ በኪራይ መረከቦ ይታወሳል፡፡

ከተከራዩት የኪራይ ክፍያ ገንዘብ ላይ ከዋና ዕዳ፣ ከወለዱና ከአገልግሎት ክፍያ በድምሩ ብር -----/-----------------/ ብቻ ከፍለው ቀሪውን ገንዘብ በውሉ መሰረትና በገቡት ግዴታ መሰረት መክፈል በሚገባዎት ቀን ስላልከፈሉ ከዋና እዳ ብር ------------ ከወለድ ብር ------------------ ከአገልግሎት ብር ------------------- ከቅጣት ብር -------------- በጠቅላላው ብር ------------/------------------------ የአክስዮን ማህበሩ ገንዘብ እንዳለብዎት ይታወቃል፡፡

ስለዚህ ይህንን ያለብዎትን እዳ እስከ -------------- ቀን -------- ዓ/ም ድረስ አጠናቀው እንዲከፍሉ እያሳሰብን ይህን ገንዘብ እስከዚህ ጊዜ ድረስ አጠናቀው የማይከፍሉ ከሆነ የካፒታል እቃውን እንዲያስረክቡ የሚደረግ ሲሆን ካለብዎት እዳ በተጨማሪ የጠበቃ አበል፣ የዳኝነት ክፍያ፣ ልዩ ልዩ ወጪና ወለድ እንዲሁም ኪሳራ ጭምር የምናስከፍላችሁ መሆኑን በጥብቅ እናሳውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፣

- ለሕግ አገልግሎት ክፍል

## V. የካፒታል ዕቃ ግዢ የውል ስምምነት

ለ ----------------------------

*የውል ስምምነት ቁጥር _*

*______/2006*

*ቀን ________ /2006 ዓ.ም*

**የካፒታል ዕቃዎች ግዢ የውል ስምምነት**

ይህ የውል ስምምነት ከዚህ በኋላ **ውል ሰጪ** ተብሎ በሚጠራው -------------------
የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አ.ማ

*አድራሻ፡-*

*ክልል*

*ከተማ፡-*

*ፋክስ ቁጥር፡-*

*ስልክ ቁጥር፡-*

*ፖስታ ሣጥን ቁጥር፡-*

**እና**

ከዚህ በኋላ **ውል ተቀባይ**_ ተብሎ የሚጠራው -----------------------

*አድራሻ፡-*

*ክልል*

*ከተማ፡-*

*ፋክስ ቁጥር፡-*

*ስልክ ቁጥር፡-*

*ፖስታ ሣጥን ቁጥር፡-*

መካከል ዛሬ _______ ቀን --------- ዓ.ም የተደረገ የውል ስምምነት ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 1</u>**
**<u>የቃላት ትርጉም</u>**

1.1 በዚህ ውል ውስጥ ተሰርቶ የሚቀርበው *ሥራ* ማለት በዚህ ውል በአንቀጽ 3 ስር የተጠቀሰውን ሰርቶ ማስረከብ ነው፡፡

1.2 የክፍያ ዋጋ ማለት በዚህ ውል አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠው ዋጋ ማለት ነው፡፡

## አንቀጽ 2
## የውሉ ዓላማ

ውል ተቀባይ ከዚህ ውል ጋር አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ዝርዝር መግለጫና ዲዛይን መሰረት የካፒታል ዕቃዎችን ማቅረብ ሥራ በውል ሰጪው በተቀመጠው መሥፈርት ሰርቶ/ ገዝቶ/ በተቀመጠለት ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ለማስረከብ ሲሆን ውል ሰጭም በበኩሉ ውል ተቀባይ የካፒታል ዕቃዎች ግዢ አቅርቦት በአንቀፅ 4.1 የተገለጸውን ጠቅላላ ዋጋ እና በአንቀፅ 4.2 መሰረት ክፍያ ለመፈፀም በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የጋራ ስምምነት ይህ ውል ተፈርሟል፡፡

## አንቀጽ 3
## ተሰርቶ የሚቀርበው የሥራ ዓይነት

ውል ተቀባይ ከዚህ ውል ጋር አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ዝርዝር መግለጫ መሰረት የካፒታል ዕቃዎች ግዢ አቅርቦት ሥራ በውል ሰጪ በተቀመጠው መሥፈርትና ዝርዝር በአባሪው በተገጸለው መሠረት ለሚፈለገው አገልግሎት ሰርቶ ለውል ሰጪ የሚያስረክበው የሥራ ዓይነት ነው፡፡

## አንቀጽ 4
## አጠቃላይ የክፍያ ዋጋ እና የአከፋፈሉ ሁኔታ

1. ውል ሰጪ ማሽነሪዎች፣የመለኪያ መሳሪያዎች፣ስልጠና እና የሥልጠና ዶክመንት እንዲሁም ፋሚላራየዚሽን ሥራ፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ የመጓጓዣ እንዲሁም ኢሬክሽንና ኮሚሺኒንግ ወጪዎች በሙሉ ያካተተ የካፒታል ዕቃ አምርቶ/ ከውጭ ሀገር አስመጥቶ አክስዮን ማህበሩ በሚፈልግበት ቦታ ለማቅረብ የሚያስችል አጠቃላይ ዋጋ ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ብር ----------- (በፊደል) ይሆናል፡፡ ስለሆነም ለውል ተቀባይ ብር------------- ( በአሀዝ) ለመክፈል ተስማምቷል፡፡ ሆኖም ውል ሰጪ የካፒታል ዕቃ ከሀገር ውጪ የሚያስመጣ ከሆነ ዋጋው ተጨማሪ እሴት ታክስን አይጨምርም፡፡

2. አከፋፈሉም ውል ሰጪ ይህንን ውል ሲፈራረም፡-

2.1. የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ሥራዎችን በተመለከተ

2.1.1 ውል ሰጪ ውሉን ከተፈራረመ በኋላ ለውል ተቀባይ ስራውን ለመጀመር የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ለመሸፈን ---------- (በፊደል) ጠቅላላ ክፍያ 30% ወይም ----------------- (በፊደል) ብር የቅድሚያ ክፍያ ይከፈላል፡፡

2.1.2 ሁለተኛ ክፍያ 50% ወይም የ---------------- (በፊደል) ብር ደግሞ የካፒታል ዕቃው ተጓጉዞ በውሉ በተገለጹት ቦታዎች ሲደርስ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2.1.3 ሶስተኛ ክፍያ ማለትም 18% ወይም ------------------ (በፊደል) አጠቃላይ የካፒታል ዕቃው ተከላና ኮሚሺኒንግ ሥራው ተጠናቆ ርክክብ ሲከናወን ተግባራዊ ይሆናል፡፡

2.1.4. አራተኛው ክፍያ ማለትም 2% ወይም ----------- (በፊደል) በውሉ መሠረት የጋራንቲ ጊዜው ሲጠናቀቅ ይሚከፍል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5
## የውል ተቀባይ ግዴታ

1. ውል ተቀባይ ከውል ሰጭ ጋር የካፒታል ዕቃዎች ግዢ ውልን እንደተፈራረመ 30% (ሠላሳ በመቶ) የቅድሚያ ክፍያ እንደተቀበለ ሥራውን መጀመር አለበት፡፡

2. ውል ተቀባይ የካፒታል ዕቃዎች ግዢን ከዚህ ውል ጋር አባሪ በሆነው ዝርዝር መግለጫ መሠረት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

3. ውል ተቀባይ ሥራውን በተሰጠው ጊዜ ገደብና በሚፈለገው ጥራት መሠረት አጠናቆ ለውል ሰጭ ያስረክባል፡፡

4. ውል ተቀባይ የሚያቀርበው የካፒታል ዕቃዎች ላይ እንከን መኖሩ ከውል ሰጪ ከተገለፀለት እንከኖቹን የማስተካከል ግዴታ አለበት፡፡

5. ሌሎች በውሉና በሕጉ ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች ይፈጽማል፡፡

6. ውል ተቀባይ የካፒታል ዕቃዎችን በውሉ መሠረት በጠየቀው ቦታ የማድረስ፣ የተከላና ኮሚሺኒንግ ሥራ የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 6

## የውል ሰጪ ግዴታ

1. ውል ሰጪ ለውል ተቀባይ የካፒታል ዕቃዎች ግዢ ውልን ተፈራርሞ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ የአጠቃላይ ግዢውን 30% (ሠላሳ በመቶ) የቅድሚያ ክፍያ መክፈል አለበት፡፡ አፈጻጸሙም በአንቀጽ 4(2) በተቀመጠው መሠረት ይሆናል፡፡

2. ውል ሰጪ የሚያቀርበውን የካፒታል ዕቃዎች በውል ተቀባይ በአንቀጽ 4(2) መሠረት እና የውል ሰጪ አማካሪ ድርጅት /ውል ሰጪው የወከለው አካል/ በሚፈለገው ዝርዝር መግለጫ መሠረት የቀረበ መሆኑን ሲያረጋግጥ በስራው ባቀረበው መቶኛ መሰረት የተቀመጠውን መጠን ክፍያ ውል ሰጪ ለውል ተቀባይ ክፍያ ይፈፅማል፡፡

3. ውል ሰጪ በውል ተቀባይ የሚቀርበውን የካፒታል ዕቃዎች ጥራታቸውን በሚመለከት ወል ሰጪ በሚያዘጋጀው ባለሙያዎች ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

4. ውል ሰጪ ለካፒታል ዕቃዎች ማስቀመጫ ምቹ ቦታ ያዘጋጃል፡፡

5. ሌሎች በውሉና በሕጉ ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎችን ይፈፅማል፡፡

## አንቀጽ 7

## የጉዳት ኪሣራን ስለመሸፈን

1. ከተዋዋዮች አንደኛው በዚህ ውል መሠረት በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታውን ባይወጣ ግዴታው ላልተፈጸመለት ወገን የጠቅላላ ዋጋውን 10% /አስር በመቶ/ እስከ ሚደርስ ድረስ በየቀኑ ለሚፈጠረው መዘግየት 0.01% /ዜሮ ነጥብ ዜሮ አንድ ፐርሰንት/ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ 7/ሀ/ የሚከፈለው ገንዘብ የሚሰራው ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ (notice) መስጠት ሳያስፈልግ መዘግየቱ እንደጀመረ ነው፡፡

## አንቀጽ 8

## የማስረከቢያ ቦታና ጊዜ

1. ውል ተቀባይ የሚቀርቡትን የካፒታል ዕቃዎች ከዚህ ውል ጋር አባሪ በሆነው ዝርዝር መግለጫ መሰረት በትክክል መቅረባቸውን በፅሁፍ አረጋግጦ ለውል ሰጪ ሲያቀርብ የውል ሰጪ አማካሪ ድርጅት /ውል ሰጪው የወከለው አካል/ የቀረቡትን የካፒታል ዕቃዎች በቦታው ተገኝቶ በመመልከት በሰነድ ሲያረጋግጥለት ለውል ሰጭ ያስረክባል፡፡

2. ውል ሰጪ ለውል ተቀባይ ከዚህ ውል ጋር አባሪ በሆነው ዝርዝር መግለጫ (Specification) መሠረት የተገለፀውን የካፒታል ዕቃዎች አቅርቦት ውሉ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ቢበዛ በ180 የስራ ቀናት ውስጥ ውል ተቀባይ ምርቱን/አቅርቦቱን/ አጠናቆ ለውል ሰጪ ያስረክባል፡፡

## አንቀጽ 9
## አለመግባባትን ስለመፍታት

1. አለመግባባቶች ቢፈጠሩ መጀመሪያ በሁለቱም ወገኖች መካከል በሚደረግ ወይይት እና ስምምነት በ7 ቀናት ውስጥ ችግሩን ለመፍታት ይሞክራሉ፡፡

2. ውይይቱ በ7 ቀናት ውስጥ በጋራ ስምምነት ሊፈታ ካልቻለ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ጉዳዩ የሚታይ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 10
## ውሉን ስለማቋረጥ

1. ከተዋዋዮች አንደኛው ወገን በዚህ ውል መሠረት የተቀመጡትን ግዴታዎች ካልፈፀመ ሌላኛው ወገን ጉድለቶቹ እንደተስተካከሉ የ-------- ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት በ---------- ቀን ውስጥ ውሉን ማቋረጥ ይችላል፡፡

2. ከአቅም በላይ የሆነ አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር የፍ/ብ/ሕ/አንቀጽ 1792-1793 ተሟልቶ ሲገኝ፡፡

## አንቀጽ 11

## ውልን ስለማሻሻል

1. በውል ውስጥ የተቀመጡትን ሁኔታዎች መቀየር ወይም ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውል ሰጪና ውል ተቀባይ በመወያየት የተሻለ ነው የሚሉትን የሥራ ስምምነት በማስቀመጥ ሊያሻሽሉት ይችላሉ፡፡

2. ውሉ የሚሻሻለው ውልን ለመመሥረት የተቀመጡትን መንገዶች ተከትሎ በጽሑፍ ብቻ እና ሥልጣን ባለው አካል ሲፈረም ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 12
## በዚህ ውል ስለአልተካተቱ ጉዳዮች

በዚህ ውል ስምምነት ያልተካተቱ ጉዳዮች በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 13
## ስለቅጣት

1. አንደኛው ወገን ያለአግባብ ውሉን ቢያቋርጥ ውሉን ያቋረጠው አካል አግባብ ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ የሚዳኝ ይሆናል፡፡

2. በፍ/ሕ/ቁ 1792 እና 1793 መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ከሁለቱም ወገኖች አንዱ የገጠመው እንደሆነ በኃላፊነት አይጠየቅም ሆኖም ደረሰ የተባለው ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል በ---------ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት

3. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ያጋጠመው ወገን መንስኤውን በዝርዝር በ-------- ተከታታይ ቀናት በጽሑፍ ለሁለተኛው ወገን ካላሳወቀ በስተቀር ቅጣቱን ከመክፈል አይድንም፡፡

## <u>አንቀጽ 14</u>
## <u>የውሉ ይዘት</u>

ከዚህ ውል ጋር አባሪ ተደርጎ የተያያዘው ______ገጽ ዝርዝር የሥራ መግለጫ የውሉ አካል ሆኖ ይቆጠራል፡፡

## <u>ተዋዋዮች</u>

| <u>ስለ ውል ሰጪ</u> | <u>ስለ ውል ተቀባይ</u> |
|---|---|
| ስም______________________________ | ስም__________________________ |
| ኃላፊነት __________________________ | ኃላፊነት _______________ |
| ፊርማ_______________________ | ፊርማ __________________ |
| ቀን_______________________________ | ቀን_____________________ |

## <u>ምስክሮች</u>

| <u>ስም</u> | <u>ፊርማ</u> | <u>ቀን</u> |
|---|---|---|
| 1.______________________ | ____________ | ____________ |
| 2.______________________ | _____________ | ______ |
| 3. ______________________ | ____________ | ____________ |

## *VI.* የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ)ሥራ የውል ስምምነት

*የውል ስምምነት ቁጥር ______/2006*

*ቀን _______ /2006 ዓ.ም*

## የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ)ሥራ የውል ስምምነት

ይህ የውል ስምምነት ከዚህ በኋላ ውል ሰጪ ተብሎ በሚጠራው ------------------- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አ.ማ

*አድራሻ፡-*

*ክልል*

*ከተማ/ክ/ከተማ፡-*

*ፋክስ ቁጥር፡-*

*ስልክ ቁጥር፡-*

*ፖስታ ሣጥን ቁጥር፡-*

**እና**

ከዚህ በኋላ ውል ተቀባይ_ ተብሎ በሚጠራው ------------------------------------------------------

*አድራሻ፡-*

*ክልል*

*ከተማ/ክ/ከተማ፡-*

*ፋክስ ቁጥር፡-*

*ስልክ ቁጥር፡-*

*ፖስታ ሣጥን ቁጥር፡-*

መካከል ዛሬ ጥር ________ ቀን 2006 ዓ.ም የተደረገ የውል ስምምነት ነው፡፡

## አንቀጽ 1
## የቃላት ትርጉም

1. በዚህ ውል ውስጥ ተሰርቶ የሚቀርበው ሥራ ማለት በዚህ ውል በአንቀጽ 3 ስር የተጠቀሰውን ሰርቶ ማስረከብ ነው፡፡
2. የክፍያ ዋጋ ማለት በዚህ ውል አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠው ዋጋ ማለት ነው፡፡
3. ተርንኪ ፕሮጀክት ማለት በዲዛይኑ መሰረት የወርክ ሾፕ ግንባታ'በአባሪው መሰረት ጠቅላላ ፋሲሊቲ'የሰው ኃይል ሥልጠና እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ሱፐርቫይዚንግን ያካተተ ፕሮጀክት ማለት ነው፡፡

## አንቀጽ 2
## የውሉ ዓላማ

ውል ተቀባይ ከዚህ ውል ጋር አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ዝርዝር መግለጫና ዲዛይን መሰረት የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክስብል ወርክ ሾፕ) ሥራ በውል ሰጪ በተቀመጠው መሥፈርት ሰርቶ በተቀመጠለት ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ለማስረከብ ሲሆን ውል ሰጭም በበኩሉ ውል ተቀባይ የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ) ለሚሰራው ሥራ በአንቀፅ 4.1 የተገለጸውን ጠቅላላ ዋጋ እና በአንቀፅ 4.2 መሰረት ክፍያ ለመፈፀም በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የጋራ ስምምነት ይህ ውል ተፈርሟል፡፡

## <u>አንቀጽ 3</u>
## <u>ተሰርቶ የሚቀርበው የሥራ ዓይነት</u>

ውል ተቀባይ ከዚህ ውል ጋር አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ዝርዝር መግለጫና ዲዛይን መሰረት የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ) ሥራ በውል ሰጪ በተቀመጠው መሥፈርትና ዝርዝር በአባሪው በተገጸለው መሠረት ለሚፈለገው አገልግሎት ሰርቶ ለውል ሰጪ የሚያስረክበው የሥራ ዓይነት ነው፡፡

## <u>አንቀጽ 4</u>
## <u>አጠቃላይ የክፍያ ዋጋ እና የአከፋፈሉ ሁኔታ</u>

1 ውል ሰጪ የወርክ ሾፕ ግንባታ፣ ማሽነሪዎች፣ የመለኪያ መሳሪያዎች፣ ስልጠና እና የሥልጠና ዶክመንት እንዲሁም ፋሚላራየዚሽን ሥራ፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ የመጓጓዣ እንዲሁም ኢሬክሽንና ኮሚሺኒንግ ወጪዎች በሙሉ ያካተተ ሥራ (ተርንኪ ፕሮጀክት) በ-------------ክልል/ከተማ ለማሠራት አጠቃላይ ዋጋ ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ብር------------------ (በፊደል) ይሆናል፡፡ ስለሆነም ለውል ተቀባይ ብር------------------ (በፊደል) ለመክፈል ተስማምቷል፡፡

2. **አከፋፈሉም ውል ሰጪ ይህንን ውል ሲፈራረም፡-**

   2.1 **የወርክ ሾፕ ግንባታን በተመለከተ**

2.1.1 ውል ሰጪ ይህንን ውል ሲፈራረም የወርክ ሾፕ ግንባታው ጠቅላላ ዋጋ ብር----------- (በፊደል) ሲሆን የቅድሚያ ክፍያ 30% ወይም ብር----------------- (በፊደል) ክፍያ ቫትን ጨምሮ ለውል ተቀባይ ውሉ በተፈረመ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ይከፈላል፡፡ በCheck list ዝርዝር መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

2.1.2 የሁለተኛው ክፍያ 30% (ሰላሳ በመቶ) የሥራው 30% (ሠላሳ በመቶ) መሰራቱን ሲረጋገጥ ይከፍላል፡፡

2.1.3 ሦስተኛ ክፍያ 20% የሥራው 80% መጠናቀቁ ሲረጋገጥ ይከፈላል፡፡

2.1.4 አራተኛው ክፍያ 15% የግንባታ ሥራው ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅየሚከፈል ይሆናል፡፡

2.1.5. አምስተኛው ክፍያ 5% ርክክቡ ከተካሄደ ከአንድ ዓመት በኋላ /Retention ጊዜው ሲጠናቀቅ/ የሚከፈል ይሆናል፡፡

## 2.2. ከወርክሾፕ ግንባታ ውጪ ያሉ ሥራዎችን በተመለከተ

2.2.1.ፋሲሊቲዎችና ማሽነሪዎች፣የቴስቲንግ መለኪያ መሳሪያዎች፣ ኢሬክሽንና ኮሚሺኒንግ ለዶክሜንቴሽን ዝግጅት፣ ለከቲንግ ቱልስ፣ ለግብዓት፣ ለማጓጓዣ እና ለመሳሰሉት ወጪዎች ብር----------------- (በፊደል) ጠቅላላ ክፍያ ሲሆን 30% ወይም ብር----------------- (በፊደል) የቅድሚያ ክፍያ ውሉ በተፈረመ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ይከፈላል፡፡

2.2.2 ሁለተኛ ክፍያ 50% ወይም ብር----------------- (በፊደል) ደግሞ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች የምርት ደረጃ 50% ላይ ሲደርስና ከውጭ አገር የሚሟሉ ፋሲሊቲዎች ግዢ ተፈፅሞ እቃው መጫናቸውን የሚያረጋግጥ ዶክመንት FOB/ Freight on Board/ ሲቀርብ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2.2.3 ሶስተኛ ክፍያ ማለትም 18% ወይም ብር----------------- (በፊደል) የተርንኪ ፕሮጀክት አጠቃላይ ስራ የመሳሪያ ኢሬክሽን እና ኮሚሺኒንግ

ተካሂዶ፣ስልጠና ተሰጥቶ፣ ሰልጣኞች በተገቢው መንገድ ምርት ማምረት መቻላቸው ሲረጋገጥ የሚከፈል ይሆናል፡፡

2.2.4. አራተኛው ክፍያ ማለትም 2% ወይም ብር ---------- (በፊደል) የጋራንቲ ጊዜው ሲጠናቀቅ የሚከፈል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5
## የውል ተቀባይ ግዴታ

1. ውል ተቀባይ ከውል ሰጭ ጋር በ------------ክልል/ከተማ የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ) ሥራን ውል በመፈራረም 30% (ሠላሳ በመቶ) የቅድሚያ ክፍያ በተቀበለ በአስር ቀናት ውስጥ ሥራ የመጀምር ግዴታ አለበት፡፡
2. ውል ተቀባይ በ------------ክልል/ከተማ የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ) ሥራ ከዚህ ውል ጋር አባሪ በሆነው ዝርዝር የሥራ መግለጫና ዲዛይን መሠረት የመሥራት ግዴታ አለበት፡፡
3. ውል ተቀባይ የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ) ሥራውን የሚጠቀምባቸውን አጠቃላይ ማቴሪያል በተቀመጠው መሥፈርትና ዝርዝር መሠረት አቅርቦ የመሥራት ግዴታ አለበት፡፡
4. ውል ተቀባይ ሥራውን በተሰጠው ጊዜ ገደብ አጠናቆ ለውል ሰጭ ያስረክባል፡፡
5. ውል ተቀባይ የሚሰራውን የወርክ ሾፕ ግንባታ ሥራ ሲሰራ እንከን መኖሩ ከውል ሰጪ ከተገለፀለት እንከኖቹን የማስተካከል ግዴታ አለበት፡፡
6. ሌሎች በውሉና በሕጉ ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች ይፈጽማል፡፡

## አንቀጽ 6

## የውል ሰጪ ግዴታ

1. ውል ሰጪ የሚያስገነባውን የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ)ሥራ በውል ተቀባይ በአንቀጽ 4(2) መሠረት በተቀመጠው የሥራ ፐርሰንት

መሠረት ሲያጠናቅቅና የውል ሰጪ አማካሪ ድርጅት /ውል ሰጪው የወከለው አካል/ በተገለፀው ፐርሰንት የተሠራ መሆኑን ሲያረጋግጡ በሰራው ፐርሰንት መሰረት የተቀመጠውን የፐርሰንት ክፍያ ውል ሰጪ ለውል ተቀባይ ክፍያ ይፈፅማል፡፡

2. ውል ሰጪ ከውል ተቀባይ ጋር ውል በተፈራረመ በአስር ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ከአጠቃላይ የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ) ሥራ ዋጋ ላይ 30% (ሰላሳ በመቶ) ለውል ተቀባይ ይከፍላል፡፡ አፈጻጸሙም በአንቀጽ 4(2) በተቀመጠው መሠረት ይሆናል፡፡

3. ውል ሰጪ በውል ተቀባይ የሚሰራውን የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ) ሥራዎችን ጥራታቸውን በሚመለከት ባሉት ባለሞያዎች በየዕለቱ የሚሰሩትን ሥራዎች ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

4. ውል ሰጪ ለወርክ ሾፕ ግንባታ ሥራው የተመቻቸ የግንባታ ቦታ፣ መሠረተ ልማት (መንገድ፣ መብራትና ውሃ መስመር) በተሟላ ሁኔታ ያቀርባል፡፡

5. ሌሎች በውሉና በሕጉ ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎችን ይፈፅማል፡፡

## <u>አንቀጽ 7</u>
## <u>የጉዳት ኪሣራን ስለመሸፈን</u>

1. ከተዋዋዮች አንደኛው በዚህ ውል መሠረት በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታውን ባይወጣ ግዴታው ላልተፈጸመለት ወገን የጠቅላላ ዋጋውን 10%/አስር በመቶ/ እስከ ሚደርስ ድረስ በየቀኑ ለሚፈጠረው መዘግየት 0.01% /ዜሮ ነጥብ ዜሮ አንድ ፐርሰንት/ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ 7/ሀ/ የሚከፈለው ገንዘብ የሚሰራው ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ (notice) መስጠት ሳያስፈልግ መዘግየቱ እንደጀመረ ነው፡፡

## <u>አንቀጽ 8</u>

## <u>የማስረከቢያ ቦታና ጊዜ</u>

1. ውል ተቀባይ የሚሰሩትን የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ)ሥራዎች ከዚህ ውል ጋር አባሪ በሆነው ዝርዝር መግለጫ ዲዛይን መሰረት በትክክል መሥራቱን በፅሁፍ አረጋግጦ ለውል ሰጪ ሲያቀርብ የውል ሰጪ አማካሪ ድርጅት /ውል ሰጪው የወከለው አካል/ የተከናወኑትን ሥራዎች በቦታው በመገኘት ሲያረጋግጡለት በሰነድ በማረጋገጥ ለውል ሰጭ ያስረክባል፡፡

2. ውል ሰጪ ለውል ተቀባይ ከዚህ ውል ጋር አባሪ በሆነው ዝርዝር መግለጫ (Specification) ዲዛይን መሠረት የተገለፀውን የተርንኪ ፕሮጀክት (የፍሌክሰብል ወርክ ሾፕ)ሥራ ውሉ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ቢበዛ በ180 የስራ ቀናት ውስጥ ውል ተቀባይ ግንባታውን አጠናቆ ለውል ሰጪ ያስረክባል፡፡

## አንቀጽ 9
## አለመግባባትን ስለመፍታት

1. አለመግባባቶች ቢፈጠሩ መጀመሪያ በሁለቱም ወገኖች መካከል በሚደረግ ወይይት እና ስምምነት በ7ቀናት ውስጥ ችግሩን ለመፍታት ይሞክራል፡፡

2. ለ. ውይይቱ በ7 ቀናት ውስጥ በጋራ ስምምነት ሊፈታ ካልቻለ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ጉዳዩ የሚታይ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 10
## ውሉን ስለማቋረጥ

ሀ. ከተዋዋዮች አንደኛው ወገን በዚህ ውል መሠረት የተቀመጡትን ግዴታዎች ካልፈፀመ ሌላኛው ወገን ጉድለቶቹ እንደተስተካከሉ የ-----------ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት በ-----ቀን ውስጥ ውሉን ማቋረጥ ይችላል፡፡

ለ. ከአቅም በላይ የሆነ አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር የፍ/ብ/ሕ/አንቀጽ 1792-1793 ተሟልቶ ሲገኝ፡፡

## አንቀጽ 11

## ውልን ስለማሻሻል

ሀ. በውል ውስጥ የተቀመጡትን ሁኔታዎች መቀየር ወይም ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውል ሰጪና ውል ተቀባይ በመወያየት የተሻለ ነው የሚሉትን የሥራ ስምምነት በማስቀመጥ ሊያሻሽሉት ይችላሉ፡፡

ለ. ውሉ የሚሻሻለው ውልን ለመመሥረት የተቀመጡትን መንገዶች ተከትሎ በጽሑፍ ብቻ እና ሥልጣን ባለው አካል ሲፈረም ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 12**
**በዚህ ውል ስለአልተካተቱ ጉዳዮች**

በዚህ ውል ስምምነት ያልተካተቱ ጉዳዮች በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 13**
**ስለቅጣት**

1. አንደኛው ወገን ያለአግባብ ውሉን ቢያቋርጥ ውሉን ያቋረጠው አካል አግባብ ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ የሚዳኝ ይሆናል፡፡

2. በፍ/ሕ/ቁ 1792 እና 1793 መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ከሁለቱም ወገኖች አንዱ የገጠመው እንደሆነ በኃላፊነት አይጠየቅም ሆኖም ደረሰ የተባለው ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል በ------ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት

3. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ያጋጠመው ወገን መንስኤውን በዝርዝር በ ተከታታይ ቀናት በጽሑፍ ለሁለተኛው ወገን ካላሳወቀ በስተቀር ቅጣቱን ከመክፈል አይድንም፡፡

**አንቀጽ 14**
**የውሉ ይዘት**

ከዚህ ውል ጋር አባሪ ተደርጎ የተያያዘው---------ገጽ ዝርዝር የሥራ መግለጫና ዲዛይን የውሉ አካል ሆኖ ይቀጠራል፡፡

**ተዋዋዮች**

| **ስለ ውል ሰጪ** | **ስለ ውል ተቀባይ** |
|---|---|
| ስም________________ | ስም____________________________ |
| ኃላፊነት __________ | ኃላፊነት ________________ |
| ፊርማ__________________________ | ፊርማ____________________ |
| ቀን____________________________ | ቀን______________________ |

**ምስክሮች**

| **ስም** | **ፊርማ** | **ቀን** |
|---|---|---|
| 1._______________________ | ___________________ | ______ |
| 2._______________________ | ___________________ | ______ |
| 3._______________________ | ___________________ | ______ |